የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
አዲስ አበባ – ሰኔ ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 46
ADDIS ABABA – 1st July, 1997

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ
ደንብ ........................................................ ገጽ ፭፻፵፬

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 17/1997
Council of Ministers Financial
Regulations .................................................. Page 544

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፹፱

## ስለ ፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፶፯/፲፱፻፹፱ አንቀጽ ፷፰ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪· ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩· "የቅድሚያ ክፍያ" ማለት የዋጋ ልውውጥ ያልተደረገበት እና ተቀባዩ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሚያወራርደው ክፍያ ሲሆን ፣ ውልን መሠረት በማድረግ በውሉ የተመለከተው ግዴታ ከመጠናቀቁ በፊት በየደረጃው የሚደረግን ክፍያ አይጨምርም ፤

፪· "የጨረታ ማስከበሪያ" ማለት የሥራ ተቋራጩ ጨረታውን ቢያሸንፍ ውሉን የሚፈርም ለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሚሰጠው የጨረታ ቦንድ ወይም የዋስትና መያዣ ነው ፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No.17/1997
## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS ON THE FINANCIAL ADMINISTRATION OF THE FEDERAL GOVERNMENT

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995, and Article 68 of the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No. 57/1997.

## *PART ONE*
## *General*

1. *Short title*

These Regulations may be cited as the "Council of Ministers Financial Regulations No.17/1997."

2. *Definitions*

In these Regulations:

1) "Advance" means a payment for which there is no exchange of value and that is to be accounted for by the recipient at some later date and does not include a progress payment made on account of,but before the completion of a contract.
2) *"Bid security"* means a bid bond or security deposit given by a contractor to the Federal Government of Ethiopia to guarantee entry into a contract if the contract is awarded to that contractor.

፫· "የካፒታል ወጪ" ማለት፣

ሀ) መንገዶችን ፣ሕንጻዎችን ወይም ሌሎች ግንባታዎችን ሳይጨምር መሬትን ለመያዝ፣ መልሶ ለመያዝ፣ ለማሻሻል ወይም ለማዘጋጀት፣

ለ) መንገዶችን፣ ሕንጻዎችን ወይም ሌሎች ግንባታዎችን ለመያዝ ፣ ለመሥራት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማሻሻል፣

ሐ) ተንቀሣቃሽ ወይም የማይንቀሣቀሱ ፕላንቶችን፣ መሣሪያዎችን፣ መገልገያዎችን ፣ ተሽከርካሪዎችን እና መርከቦችን ለመያዝ፣ ለመትከል ወይም ለመተካት፣

መ) ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ ሀ–ሐ የተዘረዘሩትን ለመፈጸም ወይም የኢንቨስትመንት ሥራዎችን ለመያዝ ለተደረገ ወይም ለሚደረግ ወጪ እንዲውል ለማናቸውም ሰው የቅድሚያ ክፍያ፣ዕርዳታ ወይም ሌላ ዓይነት የገንዘብ ድጋፍ መስጠት፣

ሠ) የሕግ ሰውነት በተሰጣቸው የንግድ ድርጅቶች ውስጥ የአክሲዮን ድርሻ ካፒታል ወይም የብድር ካፒታል በባለቤትነት ለመያዝ፣

ረ) ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ለተያያዘ የምክር አገልግሎት፣ የተደረገ ወጪ ነው።

፬· "ውል" ማለት ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ስም የሚያደርገውን፣

ሀ) የኮንስትራክሽን ሥራ፣

ለ) የዕቃ አቅርቦት፣

ሐ) የአገልግሎት ፣ ወይም

መ) የኪራይ ውልን ይጨምራል።

፭· "የውል ማስከበሪያ" ማለት፣

ሀ) የሥራ ተቋራጩ በውሉ መሠረት ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት ለማስተካከል በሥራ ተቋራጩ ስም ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሚሰጥ፣

፩· የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የደረሰበትን ጉዳት ለመካስ፣ወይም

፪· በክፍያ ቦንዱ ወይም በአፈጻጸም ቦንዱ በተመለከቱት ቃሎችና ሁኔታዎች መሠረት የውሉን አፈጻጸም ለማጠናቀቅ የሚውል የክፍያ ቦንድ ወይም የአፈጻጸም ቦንድ፣ ወይም

ለ) በውሉ ግዴታ በተገባባቸው ቃሎችና ሁኔታዎች መሠረት የሚፈፀም ለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን የሥራ ተቋራጩ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሚሰጠው የዋስትና መያዣ ነው።

፮· "የጥበቃ ኃላፊነት" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ኃላፊው በወከለው የሥራ መሪ፣ የመንግሥት ንብረት እስከሚወገድ ወይም ከመዝገብ እስከሚሠረዝ ወይም በሌላ ሠራተኛ ወይም መሥሪያ ቤት ጥበቃ ሥር እንዲውል እስከሚተላለፍ ድረስ የመንግሥትን ንብረት ለመያዝና ለመጠበቅ፣ ለአንድ የመንግሥት ሠራተኛ የሚሰጥ ኃላፊነት ነው። ይህም ኃላፊነት ከገንዘብ ሚኒስትር በሚወጣ መመሪያ በተመለከተው መሠረት መዝገብ የመያዝ ኃላፊነትንም ሊጨምር ይችላል፣

፯· "ዕዳን ማስተላለፍ" ማለት ዕዳን የመክፈል ኃላፊነትን ከአንድ ሰው ፣ ድርጅት ወይም አገር ወደሌላ ማስተላለፍ ሲሆን፣ በባለዕዳዎች ወይም በባለገንዘቦች መካከል የሚደረገውን ማስተላለፍ የሚመለከት ሊሆን ይችላል፣

3. *"Capital Expenditure"* means:

(a) the acquisition, reclamation, enhancement or laying out of land exclusive of roads, buildings or other structures;

(b) The acquisition, construction, preparation, enhancement or replacement of roads, buildings and other structures;

(c) the acquisition, installation or replacement of movable or immovable plant, machinery and apparatus, vehicles and vessels;

(d) the making of advances, grants or other financial assistance to any person towards expenditure incurred or to be incurred by him/her on the matters mentioned in paragraphs (a) to (c) above or in the acquisition of investments; and

(e) the acquisition of share capital or loan capital in any body corporate.

(f) Any associated consultancy costs of the above.

4) "Contract" includes:

(a) a construction contract;

(b) a goods contract;

(c) a service contract; or

(d) a lease

entered into on behalf of the Federal Government of Ethiopia by a public body.

5) "Contract security" means

(a) a payment bond or a performance bond given on behalf of a contractor to the Federal Government of Ethiopia to make good on any default by the contractor under the contract by:

(i) compensating the Federal Government of Ethiopia therefore, or

(ii) completing the performance of the contract to the extent required by the terms and conditions of the payment bond or performance bond, or

(b) a security deposit given by the contractor to the Federal Government of Ethiopia to secure the performance of the contract to the extent required by the terms and conditions of the contract.

6) "Custodial Responsibility", means the responsibility conferred on a government employee by the head of a public body or his or her delegated manager to protect and maintain public property, until either its disposal or deletion or its transfer to the custody of another employee or organization. This reponsibility may also include the record keeping required under the directives of the Minister of Finance;

7) "Debt assignment" means the transfer of the responsibility for a debt from one person, organization or country to another. It may refer to a transfer from one debtor to another or one creditor to another;

፰· "መሠረዝ" ማለት የመንግሥትን ንብረት እና ዋጋውን ከመዝገብ እንዲሰረዝ ማድረግ ነው፤

፱· "ማስወገድ" ማለት የመንግሥትን ንብረት በሽያጭ ወይም በዝውውር ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ወይም እንዲጠፋ ማድረግ ነው፣

፲ "አስቸኳይ" ማለት ሊታሰቡ የማይችሉ የተያያዙ ሁኔታዎች ወይም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድን የሚጠይቅ የእነዚሁ ውጤት ነው፣

፲፩· "የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ" ማለት ለዕቃ አቅርቦት፣ አገልግሎት ለማግኘት እና በመገልገያዎች ለመጠቀም ተጠቃሚዎች ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚያደርጉት ክፍያ ሲሆን መቀጫን አይጨምርም፤

፲፪· "ቋሚ ንብረት" ማለት ግዙፋዊ ሀልዎት ያለውና የተናጠል ዋጋው ብር ፪፻ እና ከዚያ በላይ የሆነ ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚኖረው እና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ንብረት ሲሆን፣ እንደ የቢሮ ዕቃ፣ ኮምፒውተር፣ ከባድ መሣሪያ፣ ተሽከርካሪ፣ መርከብ፣ አውሮፕላን፣ ሕንፃ፣ መንገድ ፡ የፍሳሽ መስመር፣ ድልድይ፣ መስኖ እና ግድብ የመሳሰሉትን ይጨምራል፤

፲፫· "የፋይናንስ ዕቅድ" የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ) ከማክሮ ኤኮኖሚያዊ ግምት ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ፀንቶ ባለው የግብር ማስከፈያ ምጣኔ መሠረት ይሰበሰባል ተብሎ የታሰበውን የመንግሥት ገቢ፤

ለ) የፖሊሲ ለውጥ ባለተደረገበት ሁኔታ በሚሠራ የማክሮ–ኤኮኖሚያዊ ዕቅድ ታክስ ካልሆኑ የመንግሥት ገቢዎች (ከመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅቶች የዘቀጠ ትርፍ፣ ከክፍያዎች፣ ከተጠቃሚዎች ከሚሰበሰብ ዋጋ ወ·ዘ·ተ) ይሰበሰባል ተብሎ የታሰበውን ገቢ፤

ሐ) ከፍተኛ የግብር ምጣኔ በመጣል፣ የተለየ የግብር ሥርዓት በመዘርጋት ወይም በግብር አሰባሰብ ረገድ የተቋም ወይም የአስተዳደር መዋቅር ማሻሻያ በማድረግ በተጨማሪነት ሊሰበሰብ የሚችለውን የገቢ ግምት፤

መ) በመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅቶች የፖሊሲ ማዕቀፍ፣ በመንግሥት ክፍለ–ኤኮኖሚ የዋጋ ትመና ፖሊሲ ፡ በማኅበራዊ አገልግሎቶች ክፍያዎች ላይ ለውጥ በመደረጉ ምክንያት ይገኛል ተብሎ የሚታሰበውን ተጨማሪ ገቢ፤

ሠ) ከአገር ውስጥ እና ከውጭ አገር ምንጮች በብድር እና በእርዳታ ሊገኝ ይችላል ተብሎ የሚታሰበውን ገቢ፤

ረ) የመደበኛ እና የልማት ወጪን ግምት።

፲፬· "የውስጥ ኦዲት" ማለት የተዘረጉ የቁጥጥር ሥርዓቶችን እና የሥራ ክንዋኔዎችን በሚመለከት ምክር ለመስጠት እንዲያገለግል የሚቋቋም የአስተዳደር እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ ማናቸውንም የሥራ ክንውን በትክክልና ሚዛናዊነቱን በጠበቀ ሥርዓትና ዘዴ ከማንኛውም ሁኔታ ነፃ ሆኖ የመገምገም ተግባር ነው፤

8) *"Deletion"* means the removal of public property and its value from the records;

9) *"Disposal"* means the sale or transfer of public property to another party or scrap of public property;

10) "Emergency" *means an unforeseen combination of circumstances or the resulting state that calls for immediate action;*

11) *"Fees and Charges"* means a payment made by users to public bodies for the supply of goods, rendering of services and use of facilities; and does not include fines and penalties;

12) *"Fixed Asset"* means tangible asset costing Birr 200 or more that is in operational use and that has a useful economic life of more than one year, such as furniture, computers, heavy equipment, vehicles, ships and aircraft, buildings, roads, sewers, bridges, irrigation systems, dam;

13) *"Fiscal Plan"* includes:

(a) Revenue forecasts at existing rates of taxation consistent with the macroeconomic assumptions;

(b) Forecast of non-tax revenues (surplus of public enterprises, fees, user charges, etc.) based on macroeconomic projections but without any changes in policy;

(c) Estimation of additional revenues which may be mobilized by, for example, higher tax rates, a different tax structure, or institutional and administrative reforms in tax collection;

(d) Estimation for additional income resulting from changes in the policy framework for public enterprises, public sector pricing policy charges in the social sectors, etc;

(e) Estimates of resources available from domestic and external borrowing and grants.

(f) Projections of current development expenditure.

14) *"Internal Audit"* means a systematic, independent and appraisal of all operations, including administrative activities, for purposes of advising management practices and controls;

፲፭· "የውስጥ ቁጥጥር" ማለት የመንግሥትን ሀብት ከጥፋት ለመከላከል፣ የሂሣብ መረጃዎችን ወቅታዊነት፣ ትክክለኛነት እና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ፣ የሥራ ክንውንን ብቃት ለማሳደግ እና ደንቦች እና መመሪያዎችን መከበራቸውን ማረጋገጥ የሥራ አመራሩ የሚከተለው የአደረጃጀትና የሥራ አፈጻጸም ሥርዓት ነው፡

፲፮· "የሕይወት ዘመን ሥርዓት" ማለት ከመንግሥት ንብረት ጋር የተያያዙ ተግባሮች እና ወጪዎችን ማለትም የማቀድ፣ የመያዝ ፣የመረከብ፣ የመጠቀም፣ የጥገና፣ የፍጆታ ወይም የማስወገድ ወይም ከመዝገብ የመሠረዝ ተግባራትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመንግሥት ንብረት አስተዳደር እና ቁጥጥር ብቃት ባለው መንገድ እንዲመራ ማድረግ ነው፤

፲፯· "የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ" ማለት ምልክት በማድረግ ወይም ያለምልክት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ በመተላለፉ ምክንያት ለተላለፈለት ሰው የባለቤትነት መብት የሚያስገኝ የገንዘብ ሰነድ ነው፤

፲፰· "በየደረጃው የሚደረግ ክፍያ" ማለት የውሉ አፈጻጸም ሙሉ በሙሉ ከመጠናቀቁ በፊት በከፊል ለተፈፀመው የውሉ ክፍል በውሉ ቃሎች መሠረት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ወይም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ስም የሚፈፀም ክፍያ ነው፡

፲፱· "የሚያዝ ገንዘብ" ማለት በውሉ መሠረት በሥራ ተቋራጩ ከሚጠየቀው በየደረጃው የሚደረግ ክፍያ ውስጥ የውሉ አፈጻጸም እስከሚጠናቀቅ እና ሥራ ተቋራጩ ለንዑስ ሥራ ተቋራጮች ክፍያ መፈፀሙ እስከሚረጋገጥ ድረስ ለሥራ ተቋራጩ ሳይከፈል የሚቆይ ሂሣብ ነው።

፳· "የዋስትና መያዣ" ማለት፡
- ሀ) የሀዋላ ሰነድ ሆኖ
  - ፩· ለገንዘብ ሚኒስቴር የሚከፈል ፡ እና
  - ፪· በታወቀ የገንዘብ ተቋም የተረጋገጠ ወይም በታወቀው የገንዘብ ተቋም በራሱ ስም የወጣ፣
- ለ) በመንግሥት ዋስትና የተሰጠበት ቦንድ ወይም
- ሐ) በመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል እና በገንዘብ ሚኒስቴር የፀደቀ ሌላ ተመሣሣይ ዋስትና ነው።

፳፩· "አላቂ ዕቃ" ማለት ከቋሚ ዕቃ ውጪ የሆነ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ሲሆን፣ በባህሪው ከተገዛበት ጊዜ ጀምሮ ለአንድ ዓመት ጥቅም ላይ የሚውል እና ዋጋው ከብር ፪፻ በታች የሆነን ንብረት ይጨምራል፡

፳፪· "የአቅራቢዎች ዝርዝር" ማለት በገንዘብ ሚኒስቴር ወይም በሌላ ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚቋቋም እና የሚጠበቅ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጨረታ ተወዳዳሪነት ሊቀበሉዋቸው የሚችሉትን አቅራቢዎች ስም እና አድራሻ የሚይዝ ዝርዝር ነው።

## ክፍል ሁለት
## የፋይናንስ ኃላፊነት

፫· የገንዘብ ሚኒስትር ኃላፊነት

የገንዘብ ሚኒስትር፡

፩· በዚህ ደንብ በዝርዝር እንደተቀመጠው በመንግሥት የፋይናንስ ሥራዎች ሁሉ የመንግሥትን የፋይናንስ ፖሊሲዎች የሚመለከቱ ዝርዝር መመሪያዎችን ያወጣል፣ ያሠራጫል፡

15) *Internal Control"* means the plan of organization and all the coordinated methods and measures adopted by management to safeguard asset, ensure the timeliness, accuracy and reliability of accounting data, promote operational efficiency and maintain adherence to regulations and directives;

16) *"Life-Time Approach"* means the effective management and control of public property by taking into account all associated activities and costs. namely, planning, acquistion, receipt, use, maintenance, consumption or disposal or deletion of public property;

17) *"Negotiable security"* means a financial instrument which is transferable from one person to another by being delivered with or without endorsement so that the title passes to the transferee;

18) *"Progress payment"* means a payment made by or on behalf of the Federal Governemnt of Ethiopia under the terms of a contract after the performance of the part of the contract in respect of which the payment is made but before the performance of the whole contract;

19) *"Retention"* means a portion of the progress billings called for under the terms of a contract that is not payable to the contractor until the contract has been completed and all subcontractors have been paid by the contractor.

20) *"Security deposit"* means:
- (a) a bill of exchange
  - (i) that is payable to the Ministry of Finance, and
  - (ii) that is certified by an approved financial institution or drawn by an approved financial institution on itself,
- (b) a government guranteed bond, or
- (c) such other security as may be deemed appropriate by the public body and approved by the Ministry of Finance.

21) *"Supplies"* means all public property other than fixed assets. It includes all assets that will be used within one year of purchase and costing less than Birr 200.

22) *"Suppliers' list"* means a list that is established and maintained by the Ministry of Finance or by another authorized public body which sets out the names and addresses of suppliers from whom public bodies may solicit bids.

## *PART TWO*
## *FINANCIAL RESPONSIBILITY*

3. *Responsibilities of the Minister of Finance*

The Minister of Finance shall:

1) Formulate and distribute Directives that detail the Governments financial policies in all areas of the Government finances as detailed in these Regulations;

፪· በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የውስጥ ኦዲት አሰራር ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ተገቢ የሆኑ የሥራ ደረጃና የሥነ ምግባር መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ይይዛል፣

፫· የፊሲካል ፕላን ያዘጋጃል።

፬· <u>የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ኃላፊነት</u>

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር፣

፩· የካፒታል ወጪ ግምቶችን የማቀናጀት፣

፪· የማክሮ ኤኮኖሚን ማዕቀፍ የማዘጋጀት፣

፫· የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራምን የማስፈጸም፣

፬· ለክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት።

፭· <u>የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ኃላፊነት</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃለፊዎች በኃላፊነታቸው ሥር የሚገኘው የመንግሥት ሀብት ለተገቢ እና አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ለፀደቀ ዓላማ ብቻ መዋሉን እንዲሁም አጠቃቀሙ ቁጠባን፣ ብቃትን እና ውጤታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈፀሙን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። ከዚህ በላይ በተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የፋይናንስ ኃላፊነት የሚከተሉትን ይጨምራል፣

፩· በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ የተዘረጋው የአሠራር ሥርዓት በትክክል መሥራቱን ያረጋግጣሉ፣

፪· ለበታች ሠራተኞቻቸው የውክልና ሥልጣን ይሰጣሉ፣

፫· የመንግሥት ገንዘብ በመቀበልና በመክፈል ተግባር እንደዚሁም በግዢ አፈጻጸም ለተሠማሩት የመንግሥት ሠራተኞች የመፈረም ሥልጣን ይሰጣሉ፣

፬· በመሥሪያ ቤቱ የተቋቋመው የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ተገቢና በቂ የሰው ኃይል ያለው መሆኑን፣ የውስጥ ኦዲትን ውጤታማ ፈጣንና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ማከናወኑን ያረጋግጣሉ፣

፭· በመሥሪያ ቤቱ የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት እያንዳንዱ ሠራተኛ ኃላፊነቱን ለይቶ ማከናወን የሚያስችል አስፈላጊ የሥራ ክፍፍል የተደረገበት መሆኑን ፣ ተገቢው ሥልጠና እና ችሎታ ያላቸው ሠራተኞች መመደባቸውን ያረጋግጣሉ፣

፮· የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁን፣ ይህንን ደንብና የገንዘብ ሚኒስቴር የሚያወጣቸውን የፋይናንስ መመሪያዎች የተሟላ የሚያደርጉና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን የተለየ ሁኔታ የሚመለከቱ ዝርዝር የሥራ አፈጻጸሞችን የሚያሳዩ የውስጥ መመሪያዎች ያወጣሉ፣

፯· ወቅታዊ እና አግባብ ያለው አስተማማኝ የፋይናንስ መረጃና ትንታኔ መዘጋጀቱን እና መሠራጨቱን ያረጋግጣሉ፣

፰· የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁን፣ ይህንን ደንብ እንዲሁም አዋጁን መሠረት በማድረግ የተዘረጋውን የአሠራር ሥርዓት በመከተል ተግባራቸውን ማከናወናቸውን፣ የውስጥ ኦዲት ጊዜውን ጠብቆ መፈፀሙን ያረጋግጣሉ።

2) Develop and maintain appropriate standards of work and conduct for application throughout all public bodies internal audit functions;
3) prepare fiscal plan.

4. *Responsibilities of the Minister for Economic Development and Cooperation.*

The Minister for Economic Development and Cooperation shall be responsible for:

1) Coordinating capital expenditure estimates;
2) Preparation of macro-economic framework;
3) Implementation of the Public Investment Programme;
4) preparation of estimates of regional subsidies.

5. *Responsibilities of Heads of Public bodies.*

Head of Public Bodies have the duty to ensure that all of the resources for which they are responsible are used only for proper and approved purposes, and that they are used in the most economical, efficient and effective way. Without limiting the generality of the foregoing, the financial responsibilities of head of public bodies shall include but are not limited to:

1) ensuring that the system developed within the public body is functioning well;
2) issuing delegations of authority to subordinates;
3) establishing signing authorities for all employees involved in the processes of receiving and disbursing public money and in procurement;
4) ensuring that the internal audit system is appropriately staffed with trained and qualified manpower and that internal audits are carried out efficiently, effectively and economically;
5) ensuring that sufficient numbers of appropriately trained employees are assigned to perform discrete function such that proper separation is maintained in the internal control system;
6) developing internal directives and procudures which complement the Financial Administration Proclamation, these Regulations and any financial directives of the Ministry of Finance, which are unique to the particular public body;
7) ensuring that timely, relevant and reliable financial information analysis is prepared and disseminated;
8) ensurig that the employees of the public body are performing their duties in compliance with the Financial Administration Proclamation, these Regulations and procedures laid down in accordance with the Proclamation; and that the internal audit is carried out timely;

፮· <u>የውስጥ ኦዲት ኃላፊነት</u>

የእያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የውስጥ ኦዲት የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል ፤

፩· የመሥሪያ ቤቱ ገንዘብና ንብረት በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ምርመራ ያካሂዳል፡ የምርመራውን ሪፖርት ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል ፤

፪· የመንግሥት መሥሪ ቤቱን ፍላጐት በተለይ የሚያሟሉ የኦዲት ፕሮግራሞች ሥርዓቶች ያዘጋጃል ፤

፫· በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ አግባብ ያላቸው የውስጥና የውጭ መመሪያዎችና ሥርዓቶች ምን ያህል ተፈጻሚ እንደተደረጉ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ለመመዘንና ለአስተዳደሩ ሪፖርት ለማቅረብ የሚያስችል ሥርዓት ያዘጋጃል ፤ እና

፬· የተለመደው የውስጥ አሠራርና ቁጥጥር ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ኤኮኖሚያዊ ለመሆኑ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ለአስተዳደሩ ምክር ይሰጣል።

## ክፍል ሦስት
## የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ዝግጅት ፤ አቀራረብ እና መፅደቅ

፯· <u>መርህ</u>

፩· የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም በኤኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር በሚሰየሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚዘጋጅ የተከታታይ ሦስት ዓመታት የካፒታል ወጪ የፋይናንስ ዕቅድ ነው።

፪· ማናቸውም የካፒታል ወጪ በመንግሥት የኢንቨስትመንት ፕሮግራም ውስጥ መታየት አለበት።

፰· <u>የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ዝግጅት እና አቀራረብ</u>

የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም የኤኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር በዓመታዊው የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ጥሪ ደብዳቤ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት።

፱· <u>የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም የጊዜ ሠሌዳ</u>

የኤኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ከገንዘብ ሚኒስትር ጋር በመመካከር የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራምን የጊዜ ሰሌዳ የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

፲· <u>የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ስለማፅደቅ</u>

፩· የግምገማው ሥራ ከተጠናቀቀ እና አስፈላጊ የሆነው ማጣራት ከተከናወነ እንዲሁም ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ጋር የሚደረገው ውይይት ከተጠናቀቀ በኋላ የኤኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትሩ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ታይቶ እንዲደገፍ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል።

፪· በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተደገፈው የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይቀርባል።

6. *Responsibilities of Internal Audit*

The Internal Audit of Public bodies shall be responsible for:

1) conducting Internal Audit at specific intervals to ascertain that public money and property are used for intended purposes, and submitting audit reports to the head of the public body;
2) developing audit programmes and audit procedures which are specifically designed to meet the requirements of the public body;
3) developing a monitoring system which will, at regular intervals, test and report to management on the public body's compliance with the applicable internal and external directives and procedures; and
4) advising management, at regular intervals, on its internal practices and controls and on whether they are efficient, effective and economical.

## PART THREE
## PUBLIC INVESTMENT PROGRAM PREPARATION, SUBMISSION AND APPROVAL

7. *Principle*
   1) The Public Investment Program is a three year rolling financial plan of capital expenditure which is to be prepared by the public bodies designated by the Ministry of Economic Development and Cooperation.
   2) All capital expenditures shall be included in the Public Investment Program.
8. *Preparation and Submission of the Public Investment Program*

   The Public Investment Program will be prepared and submitted in accordance with the guidelines prescribed by the Ministry of Economic Development and Cooperation in its annual Public Investment Program call letter.
9. *Public Investment Program Calendar*

   The Minister of Economic Development and Cooperation shall issue directives on Public Investment Program Calendar in consultation with the Minister of Finance.
10. *Approval of the Public Investment Program*
    1) Upon completion of evaluations and any necessary revisions and discussions with the heads of public bodies, the Minister of Economic Development and Cooperation shall present the Public Investment Program to the Council of Ministers for review and recommendation.
    2) The Public Investment Program recommended by the Council of Ministers shall be submitted to the Council of People's Representatives for its approval.

፲፩· ልዩ ሥልጣን
ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ጥሪ ደብዳቤ በሚገለፀው ቀን ካላቀረበ የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር በመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ውስጥ ምን ሊካተት እንደሚገባ ይወስናል።

## ክፍል አራት
## የበጀት ግምት ዝግጅት፡ አቀራረብ እና መፅደቅ

፲፪· መርህ
፩· የገቢ እና የወጪ በጀት ግምት የሚዘጋጀው ለተከታዩ የበጀት ዓመት መሆን አለበት።
፪· በመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ካልፀደቀ በስተቀር ማናቸውም የካፒታል ወጪ በካፒታል በጀት ውስጥ ሊጠቃለል አይችልም።
፫· በካፒታል በጀት ውስጥ ቀደምትነት የሚወሰነው በመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም የተመለከተውን ቀደምትነት መሠረት በማድረግ ይሆናል።
፬· በገቢው መጠቀም እንዲችል የተፈቀደለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲኖር፡ የዚህ ዓይነቱ ገቢ ለመሥሪያ ቤቱ በተፈቀደው የገቢ እንዲሁም የወጪ በጀት ድምር ውስጥ መጠቃለል ይኖርበታል፤ የተጣራ ሂሣብን ማሳየት አይፈቀድም።

፲፫· የበጀት ዝግጅት እና አቀራረብ
፩· የበጀት ግምት የሚዘጋጀው እንደአግባብነቱ የገንዘብ ሚኒስትር ወይም የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር በዓመታዊው የበጀት ጥሪ ደብዳቤ የሚያስታውቁትን ጣሪያ እና የበጀት አቀራረብ ሥርዓት መሠረት በማድረግ ይሆናል።
፪· የመደበኛ ወጪ የበጀት ግምት የዘመኑን የመጀመሪያውን ግማሽ ዓመት በጀት ጊዜያዊ ሪፖርት እንዲሁም ያለፈውን ዓመት የበጀት አፈጻጸም የሚያጠቃልል ሊሆን ይገባል።
፫· የመደበኛ እና የካፒታል ወጪ በጀት ግምቶች በመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊዎች መፈረም አለባቸው።
፬· ከታክስ እና ከሌሎችም ምንጮች የሚገኘው የገቢ በጀት ግምት ኃላፊነቱ በተሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ መፈረም አለበት።
፭· የመደበኛ ወጪ የበጀት ግምት ለግምገማ፡ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም እንደገና እንዲታይ ለማድረግ እና ለማጠቃለያ ሥራዎች ለገንዘብ ሚኒስቴር መቅረብ አለበት።
፮· የካፒታል ወጪ የበጀት ግምት ለግምገማ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም እንደገና እንዲታይ ለማድረግ እንዲሁም ለማጠቃለያ ሥራዎች ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር መቅረብ አለበት።
፯· ከታክስ እና ከሌሎችም ምንጮች የሚገኘው የገቢ በጀት ግምት ኃላፊነቱ በተሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አማካኝነት ለገንዘብ ሚኒስትሩ መቅረብ አለበት።
፰· የበጀት ግምት ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተከታዩ የበጀት ዓመት በዓይነት አገኛለሁ ብሎ የሚጠብቀውን እርዳታ ግምት፡ በዓይነት የሚገኘውን እርዳታ ዓይነት፡ በገንዘብ ያወጣል ተብሎ የሚገመተውን ዋጋ ከተሟላ ዝርዝር ጋር የሚይዝ መሆን አለበት።

11. *Discretion*
If a public body fails to submit its Public Investment Program by the specified date in the call letters, the Minister of Economic Development and Cooperation shall use its own discretion as to what shall be included in this Public Investment Program.

## *PART FOUR*
## *BUDGET ESTIMATES-PREPARATION, SUBMISSION AND APPROVAL*

12. *Principle*
1) Budget Estimates of expenditures and revenues shall be prepared for the coming fiscal year.
2) The priorities established in the Public Investment Program set the priorities of the capital budget.
3) No capital expenditure shall be included in the capital budget if it has not been approved in the Public Investment Program.
4) Where a public body is permitted to retain and expend its revenues, such revenues shall be included in both its revenue and expenditure appropriation totals; no netting is permitted.

13. *Preparation and Submission of budget*
1) Budget Estimates shall be prepared in accordance with the financial limits and formats prescribed by the Minister of Finance and the Minister of Economic Development and Cooperation in their annual budget call letters.
2) Budget Estimates of recurrent expenditures shall include a report of preliminary results of the first half of the current year and previous year performance.
3) Budget Estimates of recurrent and capital expenditures shall be signed by the Heads of the public bodies.
4) Budget Estimates of revenues from taxation and other sources shall be signed by the Heads of the responsible public bodies.
5) Budget Estimates of recurrent expenditures shall be presented and submitted to the Ministry of Finance for evaluation, any necessary revisions and consolidation.
6) The Budget Estimates of capital expenditures shall be submitted and presented to the Ministry of Economic Development and Cooperation for evaluation any necessary revisions and consolidation.
7) Budget Estimates of revenues from taxation and other sources shall be presented and submitted by the responsible public bodies to the Ministry of Finance.
8) Budget Estimates shall include Estimates of all aids-in-kind that the public body expect to receive in the upcoming fiscal year including full details of the nature of the aid-in-kind and its estimated monetary value.

፲፬· የበጀት ግምትን ስለማፅደቅ

፩· የበጀቱ ግምት ከተገመገመ እና አስፈላጊ የሆነው ማጣራት ከተከናወነ እንዲሁም ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ጋር የሚደረገው ውይይት ከተጠናቀቀ በኋላ የገንዘብ ሚኒስትሩ የተጠቃለለው የመደበኛ እና የካፒታል ወጪ በጀት ግምት ታይቶ እንዲደገፍ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል።

፪· በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተደገፈው የበጀት ግምት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይቀርባል። የበጀቱ ግምት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀ በኋላ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ይወጣል ፤ እንዲሁም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የፀደቀውን በጀት እንዲያውቁ ይደረጋል።

፲፭· የበጀት የጊዜ ሠሌዳ

የገንዘብ ሚኒስትር ከኤኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ጋር በመመካከር የበጀት የጊዜ ሰሌዳን የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

፲፮· ልዩ ሥልጣን

ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የገንዘብ ሚኒስትር በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ መሠረት በሚወስነው የጊዜ ሠሌዳ የበጀቱን ግምት ካላቀረበ የገንዘብ ሚኒስትር እና የኤኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር የራሳቸውን ልዩ ሥልጣን በመጠቀም በበጀቱ ግምት ውስጥ ምን መካተት እንደሚገባው ይወስናሉ።

## ክፍል አምስት
## የበጀት አፈጻጸም

፲፯· የበጀት ዝውውር

፩· የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፀደቀ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የአደረጃጀት ለውጥ ምክንያት ወይም ለመንግሥት ዓላማዎች ግብ መድረስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከመደበኛ ወደ ካፒታል በጀት ዝውውር እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል።

፪· ከደመወዝ፣ ለሠራተኛ ከሚከፈል የአጭር ጊዜ የጉልበት ወይም የአገልግሎት ዋጋ ወይም ከአበል ወደ ሌላ መደበኛ ወጪ በጀት ማዘዋወር የሚቻለው ዝውውሩን የገንዘብ ሚኒስትር ሲያፀድቀው ብቻ ይሆናል።

፫· ከሌሎች መደበኛ ወጪዎች በጀት ወደ ደመወዝ፣ ለሠራተኛ ወደሚከፈል የአጭር ጊዜ የጉልበት ወይም የአገልግሎት ዋጋ እና አበል ማዘዋወር አይቻልም።

፲፰· የበጀት ቁጥጥር

፩· የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ከገንዘብ ሚኒስትሩ በሚተላለፈው መመሪያ መሠረት ለእያንዳንዱ የበጀት ርዕስ፣ ንዑስ ርዕስ እና ለእያንዳንዱ የካፒታል ፕሮጀክት የተፈቀደውን ዝውውር እና ድልድል የሚያሳይ የበጀት መዝገብ መያዝ አለባቸው።

፪· የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ከገንዘብ ሚኒስትሩ ወይም ከኤኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትሩ በሚተላለፍ መመሪያ መሠረት መንግሥት በበጀት ላይ በማዕከላዊነት ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችለውን መረጃ መስጠት አለባቸው።

14. *Approval of Budget Estimates*

1) Upon completion of evaluations and any necessary revisions and discussions with the Heads of public bodies, the Minister of Finance shall present the compiled Budget Estimates of recurrent and Budget Estimates of capital expenditures to the Council of Ministers for review and recommendation.

2) The Budget Estimates recommended by the Council of Ministers shall be submitted to the Council of Peoples' Representatives. After approval, the Budget Estimates shall then be published in the Negarit Gazetta and notification shall be made on the approved estimates to the heads of public bodies.

15. *Budget Calendar*

The Minister of Finance shall issue directives on budget Calendar in consultation with the Minister of Economic Development and Cooperation.

16. *Discretion*

If a public body fails to submit its Budget Estimates inaccordance with Article 15 of this Regulations, the Minister of Finance and Minister of Economic Development and Cooperation shall use their own discretion as to what shall be included in these Budget Estimates.

## *PART FIVE*
## *BUDGET EXECUTION*

17. *Budget Transfer*

1) The Council of Ministers may grant transfers from recurrent to capital appropriations when necessitated by an approved reorganization of a public body, or where it can be demonstrated that it is clearly beneficial to the achievement of government objectives.

2) Transfers from salaries, wages and allowances to another recurrent expenditure budget shall be subject to the approval of the Minister of Finance.

3) No transfer shall be allowed from other recurrent expenditure budget to salaries, wages and allowances.

18. *Budgetary Control*

1) Subject to directives of the Minister of Finance, the heads of public bodies shall maintain a register of appropriations, authorized transfers and allotments for each budgetary head and sub-head and for each capital project.

2) Subject to directives of the Minister of Finance and the Minister of Economic Development and Cooperation, the heads of public bodies shall provide information to enable the government to maintain necessary central controls over budgetary funds.

፲፱· ተጨማሪ በጀት

፩· አዲስ ወይም ያልታሰበ ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት የተጨማሪ መደበኛ በጀት ጥያቄ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥያቄው የገንዘብ ሚኒስትሩ የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስትሩ ይቀርባል።

፪· አዲስ ወይም ያልታሰበ ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት የተጨማሪ የካፒታል በጀት ጥያቄ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥያቄው የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ተዘጋጅቶ ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ይቀርባል፤ የጥያቄው ቅጂ ለገንዘብ ሚኒስትሩ ይተላለፋል።

፳· የበጀት መጠየቂያ

ማናቸውም የገንዘብ ዝውውር የሚጠይቅ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የበጀት መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጾችን በበቂ ቅጂ መሙላት እና ለገንዘብ ሚኒስቴር ማቅረብ አለበት።

## ክፍል ስድስት
## የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ

፳፩· ፈቃድ ስለመስጠት

የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው።

፳፪· የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ማዘዣ

ተገቢው የክፍያ ማዘዣ ሳይሞላ ማናቸውም የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም አይችልም። ስለሆነም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚፈጽሙት የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሁሉ ከገንዘብ ሚኒስቴር በሚወጣው መመሪያ መሠረት የክፍያ ማዘዣ መሙላት አለባቸው።

፳፫· ፈቃድ ስለተሰጣቸው ሰዎች ዝርዝር

፩· እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ሰነዶች እንዲፈርሙ ፈቃድ የተሰጣቸውን ሠራተኞች ስም ዝርዝር ማዘጋጀትና መያዝ አለበት።

፪· እንዲህ ያሉ የስም ዝርዝሮች ለመሥሪያ ቤቱ ሂሣብ ሹም፣ ለውስጥ ኦዲት ኃላፊ፣ እና ለገንዘብ ሚኒስቴር መተላለፍ አለባቸው።

፳፬· የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ አፈጻጸም

የመንግሥት ገንዘብ ክፍያዎች ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በጥሬ ገንዘብ፣ በቼክ፣ በሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ በባንክ ዝውውር ወይም በክፍያ ማዘዣ ይፈጸማሉ።

## ክፍል ሰባት
## የዕቃ እና የአገልግሎት ክፍያዎች

፳፭· መርህ

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን ልክ በሚወስኑበት ጊዜ የሚከተሉትን መርሆዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፣

፩· ለግብር ከፋዩ ኅብረተሰብ ፍትሀዊ ለመሆን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚያቀርቡት አገልግሎት የሚያስፈልገው የወጪ ጫና በአጠቃላዩ የግብር ከፋይ ኅብረተሰብ ላይ ከሚያርፍ ይልቅ የአገልግሎቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ በሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ላይ የሚያርፍበትን መንገድ መፈለግ እና/ወይም፣

19. *Supplementary Appropriation*

1) When the need arises, as a result of new or unforeseen requirements, proposals for supplementary appropriations for recurrent expenditures shall be submitted to the Minister of Finance in accordance with the directives of the Minister of Finance.
2) When the need arises, as a result of new or unforeseen requirements, proposals for supplementary appropriations for capital expenditures shall be submitted to the Minister of Economic Development and Cooperation in accordance with the directives of the Minister of Economic Development and Cooperation; and a copy submitted to the Minister of Finance.

20. *Budget Requisition*

Any public body which requires a transfer of funds shall complete the necessary number of copies of the Budget Request and Authorisation form in accordance with directives issued by the Ministry of Finance and forward them to the Ministry of Finance.

## PART SIX
## PUBLIC DISBURSEMENTS

21. *Authority*

Payments shall be made only if they are appropriated.

22. *Payment Vouchers*

No payment shall be made unless it is adequately vouched; and public bodies shall complete Payment Vouchers for all payments in accordance with directives issued by the Ministry of Finance.

23. *List of Authorized Persons*

1) The head of every public body shall establish and have maintained a list of employees whom he or she has authorized to sign the documents referred to in these Regulations.
2) Such lists shall be circulated to the senior financial officer of the public body, the head of the Internal Audit of the public body, and to the Ministry of Finance.

24. *Mode of Payment*

Payments shall be made by means of cash, cheque, letters of credit, bank transfers, or payment orders, in accordance with directives issued by the Ministry of Finance.

## PART SEVEN
## FEES AND CHARGES

25. *Principles*

All public bodies shall consider the following principles in establishing and maintaining fees and charges:

1) the promotion of fairness to tax payers by shifting the costs of a particular activity from taxpayers at large to the specific users who benefit most directly from that activity, and/or

፪· የዕቃዎችና የአገልግሎቶች አቅርቦት እና ፍላጐት የገበያ ዓይነት ሥርዓትን እንዲከተል በማድረግ የሀብት አጠቃቀምን ብቃት ማሳደግ።

፳፮· <u>የዕቃ እና የአገልግሎት አቅርቦትን ስለማጥናት</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን አዋጅ መሠረት በማድረግ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ውስጥ ከተጠቃሚዎች የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ ለመጠየቅ የሚቻልባቸውን ለመለየት በእንቅስቃሴዎቻቸው ላይ ጥናት ማካሄድ አለባቸው።

፳፯· <u>የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን ልክ የመወሰኛ መመዘኛዎች</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን ልክ በሚወስኑበት ጊዜ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡

፩· የዕቃና የአገልግሎት ክፍያውን ወጪ፣

፪· የዕቃና የአገልግሎት ክፍያው ገቢ በማመንጨት ረገድ ያለውን አቅም እንዲሁም ክፍያው በተጣለበት እንቅስቃሴ እና በሌሎችም የመንግሥት ተግባራት ላይ የሚኖረውን ውጤት፣

፫· ተጠቃሚዎች ከዕቃው ወይም ከአገልግሎቱ ጥራት እና ከዋጋው አንፃር ለመክፈል ያላቸውን ፈቃደኝነት እና አቅም፣

፬· ተጠቃሚዎች የዕቃዎች እና የአገልግሎቶች ጥራት እና ዋጋ አጥጋቢ ስለመሆኑ ያላቸውን አስተያየት ደረጃ፣

፳፰· <u>ማፅደቅ</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች አዳዲስ ክፍያዎችን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን አስተያየት በገንዘብ ሚኒስትር በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው ማስፀደቅ ይኖርባቸዋል።

፳፱· <u>ስለማሳወቅ</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የፀደቁ አዳዲስ የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የተደረጉና የፀደቁ ማሻሻያዎችን ዝርዝር ከሚፀኑበት ቀን ጭምር ማሳወቅ አለባቸው።

፴· <u>መመርመር</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከገንዘብ ሚኒስቴር በሚወጣው መመሪያ በሚወሰን የጊዜ ልዩነት የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎች መጠን በቂ ስለመሆኑ ግምገማ ማካሔድ አለባቸው።

## ክፍል ስምንት
## <u>የመንግሥት ገንዘብ ስለመቀበልና ገቢ ስለማድረግ</u>

፴፩· <u>የመንግሥት ገንዘብ መሰብሰብና ገቢ ማድረግ</u>

የመንግሥት ገንዘብ ለመሰብሰብ በሕግ ግዴታ የተጣለበት የእያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ለመንግሥት ገንዘብ አሰባሰብ ተግባር የተሟላና ብቃት ያለው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን እና የመንግሥት ገንዘብ በሚገባ መሰብሰቡን ማረጋገጥ አለበት።

2) the promotion of a more efficient allocation of resources by introducing a commercial-type discipline on the demand for and supply of goods and services.

26. *Survey of Activities*

Subject to the proclamation which established them all public bodies shall conduct survey of all their activities in order to determine those for which they may justifiably subject their clients or users to a fee or a charge.

27. *Criteria for Determining Level of Fees & Charges*

In determining the level of Fees and Charges all public bodies shall take into consideration the following criteria;

1) The cost of the activity in question;
2) An initial assessment of the revenue potential of the fee and its ramifications on this activity and other activities of the government;
3) The willingness and ability of users to pay in the light of the quality and value of the goods or services; and,
4) The apparent level of user satisfaction as indicated by quality and value of the goods or services.

28. *Approval*

The heads of the public bodies shall forward their recommendations for new fees and charges and changes in existing fees and charges, through the Minister of Finance, to the Council of Ministers for its approval.

29. *Publication*

All public bodies shall publish the details of all new approved fees and charges and any approved changes to existing fees and charges together with their effective dates.

30. *Review*

All public bodies shall review the adequacy of their fees and charges at intervals stated in directives issued by the Ministry of Finance.

## *PART EIGHT*
## *RECEIPT AND DEPOSIT OF PUBLIC MONEY*

31. *Collection and Deposit of Public Money*

The Head of every public body shall ensure that there is an adequate and effective internal control system for the collection functions within the public body so that all public money, which the public body is legally obliged to collect, is collected promptly.

፴፪· የመንግሥት ገንዘብ ስለመቀበል

፩· በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ስም ለሚሰበሰብ ማናቸውም ገንዘብ ተከታታይ ቁጥር ያለው የገንዘብ ሚኒስቴር ሕጋዊ ደረሰኝ መሰጠት አለበት።

፪· ለማናቸውም ተመላሽ ገንዘብ ፣ በጥሬ ገንዘብ፣ በቼክ ወይም በባንክ ዝውውር ከገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ከሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለተዘዋወረው ገንዘብ ጭምር፣ ተቀባዩ ሕጋዊ ደረሰኝ መስጠት አለበት።

፴፫· የአደራ ገንዘብ

፩· ከፍርድ ቤት ወይም አግባብ ካለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚሰጥ ትዕዛዝ መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በድርጅቶች ወይም በግለሰቦች ስም የአደራ ገንዘብ በጊዜያዊነት ተቀብለው ለማቆየት ይችላሉ።

፪· የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በአደራ የተቀበሉትን ገንዘብ የፌዴራል መንግሥቱ ሀብት ከሆነው ገንዘብ ለይተው ማስቀመጥ አለባቸው።

፴፬· በቼክ ስለሚሰበሰብ ገንዘብ

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ባንክ የሚያወጣው ቼክ ለወደፊት ባለ ቀን የሚከፈል እስካልሆነ እና ለተቀባዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤት እንዲከፈል የታዘዘ እስከሆነ ድረስ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለክፍያ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል። ተቀባይነትን ያገኘ ቼክ ወዲያውኑ "በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ገቢ ለማድረግ ብቻ (የተቀባዩን የመንግሥት መሥሪያ ቤት ስም)" የሚል አጠቃቀሙን የሚገድብ ምልክት ሊደረግበት ይገባል።

፴፭· ገቢ ስለማድረግ

፩· ማናቸውም ከገንዘብ ሰብሳቢ ወይም ከማናቸውም ሌላ ሰው የመንግሥት ገንዘብ የሚሰበስብ ወይም የሚቀበል ሰው በየቀኑ ወይም ከገንዘብ ሚኒስቴር በሚወጣው መመሪያ በሚመለከተው ልዩ አሠራር መሠረት የሰበሰበውን ገንዘብ ገቢ ማድረግ አለበት።

፪· ገቢ የሚደረግ ገንዘብ ሁሉ የበጀት ገቢ ሲሆን ገንዘቡን በሰበሰበው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የባንክ ሂሣብ ወይም በአዲስ አበባ ብሔራዊ ባንክ ወይም የብሔራዊ ባንክ በሚሰይማቸው ባንኮች በሚገኘው የገንዘብ ሚኒስቴር የባንክ ሂሳብ ወስጥ ገቢ መደረግ አለበት።

፫· ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ወይም ገንዘቡ ገቢ ለሚያደርግለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተጠቃለለ ፈንድ እንዲከፈል ያልታዘዘ ቼክ ፣ የሀዋላ ሰነድ እና የተስፋ ሰነድ ገቢ ሊደረግ አይችልም።

፴፮· ምዝገባ

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፪ እና ፴፫ መሠረት የሚደረገው የደረሰኞች ምዝገባ የሚከናወነው ከገንዘብ ሚኒስቴር በሚወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

፪· በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፴፪ ከተመለከተው የተመላሽ ወጪ በስተቀር ማናቸውም ተሰብሳቢ የመንግሥት ገንዘብ በገቢነት መመዝገብ አለበት።

፴፯· መመሪያዎች

የመንግሥት ገንዘብ የሚሰበሰብበትን እና ገቢ የሚደረግበትን ዝርዝር ሥርዐት የሚወስን መመሪያ በገንዘብ ሚኒስቴር ይወጣል።

32. *Receipt of Public Money*

1) For every sum of money collected on behalf of the Federal Government of Ethiopia, a serially numbered, official receipt of the Ministry of Finance shall be issued.

2) For every remittance received, including cash transfers from the Ministry of Finance or other public bodies, whether they are in the form of cash, cheque or bank transfer, an official receipt shall be issued to the remitter by the receiver.

33. *Temporary Custody*

1) Public bodies may receive and keep any sum of money on behalf of orgnizations or individuals for temporary custody in trust or any other reasons when they are ordered by courts or appropriate public bodies.

2) Public bodies shall keep such money seperately from receipts of money belonging to the Federal Government.

34. *Collection in Cheques*

Cheques drawn on a bank within Ethiopia may be accepted in payment, subject to directives issued by the Ministry of Finance provided they are not post-dated and are made payable to the public body to which they are tendered. If they are accepted, such cheques shall be immediately endorsed restrictively as follows: ''For Deposit Only to the Consolidated Fund (name of receiving public body)''

35. *Deposit*

1) Every person who collects or receives public money from a collector or from any other person shall deposit it daily or in accordance with the exceptions contained in directives issued by the Ministry of Finance.

2) All such deposits shall be made either in the bank account of the public body which collects it, or in the bank account of the Ministry of Finance with the National Bank in Addis Ababa or with banks designated by the National Bank.

3) Cheques not made payable to the Consolidated Fund of the Federal Government of Ethiopia or to the public body to which they are tendered, bills of Exchange and Promissory Notes are not acceptable for deposit.

36. *Recording*

1) All Recording of receipts under Articles 32 and 33 shall be done in accordance with directives of the Ministry of Finance.

2) All receipts of public money, except for Refunds of Expenditure as described in Article 32, of the Financial Administration Proclamation, shall be recorded as revenue.

37. *Directives*

Detailed procedures for the collection and deposit of public money shall be issued by the Ministry of Finance as directives.

## ክፍል ዘጠኝ
## የቅድሚያ ክፍያዎች

፴፰· ግዢ ለመፈጸም ስለሚሰጡ የቅድሚያ ክፍያዎች

፩· ግዢ ለመፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሠራተኛ የጥሬ ገንዘብ የቅድሚያ ክፍያ ሊደረግ ይችላል። ሠራተኛው እንዲህ ያለውን የቅድሚያ ክፍያ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ካልፈቀደ በስተቀር ክፍያው በተሰጠው በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ማወራረድ አለበት።

፪· የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊው ወይም ኃላፊው በጽሑፍ የወከለው ሠራተኛ የቅድሚያ ክፍያውን ከፍተኛ መጠን ይወስናል። የቅድሚያ ክፍያን ከፍተኛ መጠን ለመወሰን ምን ምን ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው ገንዘብ ሚንስቴር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፴፱· ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ ስለሚደረግ የቅድሚያ ክፍያ

፩· በተከታታይ ከሶስት ወር በላይ የውሎ አበል ክፍያ መፈጸም አይቻልም።

፪· የውሎ አበልና የመጓጓዣ አበል የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈጸማል።

፵· የአጭር ጊዜ የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ

፩· ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለመንግሥት ሠራተኛ የአጭር ጊዜ የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል።

፪· የአጭር ጊዜ የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ በተሰጠበት ወር ከሠራተኛው ደመወዝ መቀነስ አለበት።

፫· የገንዘብ ሚኒስቴር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለአጭር ጊዜ የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ የሚያውሉት ተዘዋዋሪ ሂሳብ ሊይዝ ይችላል።

፵፩· የረጅም ጊዜ የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ

ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለቋሚ የመንግሥት ሠራተኞች የረጅም ጊዜ የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል።

፵፪· የቅድሚያ ክፍያ ገደብ

የቅድሚያ ክፍያ የተሰጠው የመንግሥት ሠራተኛ የሚፈለግበትን የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ እስካላወራረደ ወይም እስካልተካ ድረስ በተመሳሳይ ምክንያት የቅድሚያ ክፍያ አይሰጠውም።

፵፫· የቅድሚያ ክፍያዎችን ስለማስመለስ

፩· የማናቸውም መንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኛ በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠውን የቅድሚያ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ሳይከፍል ወይም ሳያወራርድ ቢቀር፣ ያልተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ከጡረታ አበል በስተቀር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ለሠራተኛው ከሚከፍለው ማናቸውም ገንዘብ ላይ ሊቀነስ ወይም ሊተካ ይችላል።

## *PART NINE*
## *ADVANCES*

38. *Advances for Purchases*

1) When necessary to make purchases cash advances may be made to an employee of a public body which must be settled within seven working days after payment is received unless otherwise authorized by the Head of Public Body.

2) The maximum amounts of such advances shall be established by the head of the public body or by an officer authorized in writing by the head of the same public body. The criteria for determining the amount of such advances shall be determined in accordance with directives issued by the Ministry of Finance.

39. *Advances of Per diem and Travel Allowances*

1) No per diem shall be paid for more than 3 months.

2) Advances of per diem and travel allowances shall be made in accordance with directives issued by the Ministry of Finance.

40. *Short Term Salary Advances*

1) Short term salary advances may be granted to an employee inaccordance with directives issued by the Ministry of Finance.

2) Short term salaryadvances shall be deducted from the employee's salary in the same month in which the advance was granted.

3) Ministry of Finance may maintain a revolving fund to be used by public bodies for the payment of short term salary advances.

41. *Long Term Salary Advances*

Long term salary advances may be granted to permanent employees in accordance with directives issued by the Ministry of Finance.

42. *Restriction in Advances*

No advances of the same type may be issued to an employee of a public body unless and until all existing advances are accounted for or returned by the employee to whom they were issued.

43. *Recovery of Outstanding Advances*

1) Where any employee of a public body fails to repay or account for an advance or any portion of an advance made to him or to her in accordance with these Regulations, the outstanding amount of the advance may be recovered from any money payable to him or her by the Federal Government of Ethiopia, except for pension money payable.

፪· ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኛ በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠውን የቅድሚያ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ሳያወራርድ ወይም ሳይመልስ ቢሞት፣ ያልተመለሰው የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ ከጡረታ አበል በስተቀር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ለሠራተኛው ወራሾች ከሚከፍለው ማናቸውም ገንዘብ ላይ ሊቀነስ ወይም ሊተካ ይችላል።

፫· ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ባልተከፈሉ የቅድሚያ ክፍያዎች ላይ አስፈላጊ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል በያንዳንዱ ወር መጨረሻ ያልተከፈሉ የቅድሚያ ክፍያዎችን ሁሉ ማጣራት አለበት።

፬· ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን የሚለቁ ወይም ጡረታ የሚወጡ ሠራተኞች የመጨረሻውን ጊዜ ደመወዝ ክፍያ ከማግኘታቸው በፊት የወሰዱት የቅድሚያ ክፍያ መመለሱን ማረጋገጥ አለበት።

፭· ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበጀት ዓመቱ ካለቀ ቀጥሎ ባለው ወር የተሟላ ያልተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ ዝርዝር መግለጫ ያዘጋጃል። ይህ ዝርዝር መግለጫ ሊመለሱ የማይችሉ ያልተከፈሉ የቅድሚያ ክፍያዎችን በመለየት ሊመለሱ ያልቻሉበትን ምክንያት ከሚያሳይ አጭር መግለጫ ጋር መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ቅጁው የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሁለት ወራት ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር መላክ አለበት።

፵፬· መዛግብት

እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብን የሚመለከት ተገቢና የተሟላ የሂሣብ መዝገብ መያዝ አለበት።

፵፭· ሪፖርት ስለማቅረብ

ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በያንዳንዱ በጀት ዓመት መጨረሻ ያልተከፈሉ ማናቸውንም የቅድሚያ ክፍያዎች ሪፖርት ከተጠናቀቀው በጀት ዓመት ሂሣብ ሪፖርት ጋር ማቅረብ አለበት።

የቅድሚያ ክፍያዎች የተፈጸሙት በተያዘው የበጀት ዓመት ወይም ባለፉት ዓመታት መሆኑ ተለይቶ መታየት አለበት። በተጨማሪም፣ ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከሂሣብ መዝገብ የተፋቁትን የዚያኑ ዓመት ወይም ያለፉትን ዓመታት የቅድሚያ ክፍያዎች በሚመለከት ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

## ክፍል አሥር
## ተሰብሳቢ ሂሣቦችን፣ ግዴታዎችንና የይገባኛል ጥያቄዎችን ከመዝገብ ስለመሠረዝ

፵፮· ከመዝገብ የመሠረዝ ሥልጣን

፩· የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ኃላፊውን በመወከል ምክትል ኃላፊው ከአጣሪ ኮሚቴ በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት ከብር ፲ሺህ የማይበልጥ ገንዘብ የያዘውን እያንዳንዱን ሂሣብ ከመዝገብ የመሠረዝ ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን፣ በዚህ ዓይነት ከመዝገብ የሚሠረዘው ሂሣብ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር ፶ሺህ ሊበልጥ አይችልም።

2) Where an advance or any portion of an advance made to any employee of a public body under these Regulations remains outstanding and unaccounted for at the time of his death, the outstanding amount of advance may be recovered from any money payable by the Federal Government of Ethiopia to the heirs of employee, except for pension money payable.

3) All public bodies shall review all advances outstanding at the end of every month as the basis for taking the necessary action to clear overdue advance.

4) Every public body shall ensure that all of its employees who resign or retire are required to clear advances before they receive their last payment of salary.

5) In the month following the end of each fiscal year, each public body shall prepare a complete analysis of all outstanding advances. This analysis shall isolate all those outstanding advances which are considered to be irrecoverable and shall be supported by a brief indication of why this determination was made. A copy of this analysis shall be forwarded to the Ministry of Finance within two months of the end of each fiscal year.

44. *Records*

Every public body shall maintain appropriate and complete accounting records of all advances made by the public body.

45. *Reporting*

Subject to directives issued by the Minister of Finance, all public bodies shall report all advances outstanding at the end of every fiscal year in the Public accounts for the fiscal year just ended. This advances shall be divided according to whether they had been made in that year or in prior years. In addition, all public bodies shall report all advances written off in the fiscal year just ended according to whether these advances had been made by the public body in that year or in prior years.

## *PART TEN*
## *WRITE-OFFS OF RECEIVABLES, OBLIGATIONS AND CLAIMS*

46. *Power to Write-off*

1) The Head of a public body or the Deputy Head on behalf of the Head shall have the power of write-off upon the recommendation of a review committee in every case upto an amount of Birr 10,000 which does not exceed a total amount of Birr 50,000 in a fiscal year.

፪. የገንዘብ ሚኒስትሩ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ እና ከአጣሪ ኮሚቴ በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት ከብር ፲ሺህ የሚበልጥ ገንዘብ የያዘውን እያንዳንዱን ሂሳብ ከመዝገብ የመሠረዝ ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን፣ በዚህ ዓይነት ከመዝገብ የሚሠረዘው ሂሳብ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር ፻ሺህ ሊበልጥ አይችልም።

፫. የገንዘብ ሚኒስትሩ የአጣሪ ኮሚቴ የሚቋቋምበትን ሁኔታ በሚመለከት መመሪያ ያወጣል።

፬. እያንዳንዱ እንዲሰረዝ አስተያየት የቀረበበት ሂሳብ የያዘው ገንዘብ ከብር ፩፻ሺህ የሚበልጥ ሲሆን፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሣኔ እንዲሰጥበት ከሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ እና ከገንዘብ ሚኒስትሩ አስተያየት እንዲሁም ለውሣኔ አሰጣጥ አስፈላጊ ከሆኑ መረጃዎች ጋር ይተላለፋል።

፵፯. የሠራተኞች እና የቀድሞ ሠራተኞች የዕዳ ስረዛ

፩. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ለሠራተኞች ከተገቢው በላይ ከተከፈለ ደመወዝ ወይም ከቅጥር ጋር በተያያዘ አበል ምክንያት የሚፈለግ ማናቸውም ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ግዴታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ ወይም የዚሁ ክፍል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ካልፀደቀ በስተቀር ከመዝገብ ሊሠረዝ አይችልም።

፪. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ቢኖርም ከሥራ ከተሰናበቱ እና ሊከፈላቸው የሚገባ ማናቸውም ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ከቀድሞ ሠራተኞች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሚፈለግን ማናቸውንም ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ግዴታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ በሚመለከት ከመዝገብ የመሠረዝ መርህ ተፈጻሚ ይሆናል።

፵፰. ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

፩. እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በየወሩ መጨረሻ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን፣ ግዴታዎችንና የይገባኛል ጥያቄዎችን በሚመለከት የተሟላ መግለጫ ማዘጋጀት እና የዚሁን ግልባጭ ለገንዘብ ሚኒስቴር መላክ አለበት። ይህም መግለጫ ገቢ ሊሆኑ የማይችሉትን ተሰብሳቢ ሂሳቦች፣ ግዴታዎች እና የይገባኛል ጥያቄዎች ለይቶ የሚያሳይና ከዚህ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የተቻለበትን ምክንያት በሚዘረዝር አጭር መግለጫ የተደገፈ መሆን አለበት።

፪. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፶፫ በተሰጠ ሥልጣን መሠረት የሚወጣውን መመሪያ በመከተል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በየወሩ መጨረሻ በመዝገባቸው የሚታየውን ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ግዴታ እና የይገባኛል ጥያቄ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት የማድረግ እንዲሁም በየዓመቱ መጨረሻ በመዝገባቸው የሚታየውን ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ግዴታ እና የይገባኛል ጥያቄ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት የመንግሥት ሂሳብ ውስጥ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው።



2) The Minister of Finance shall have the power of write-off upon the recommendation of the Head of the public body and a review committee in every case where the amount is more than Birr 10,000 which does not exceed Birr 100,000 in a fiscal year.

3) The Minister of Finance shall issue directives for the establishment of a review committee.

4) In every case where there is an amount of 100,000 Birr or more proposed to be written off, the matter shall be referred to the Council of Ministers together with the recommendation of the head of the public body, the recommendation of the Minister of Finance, and all other relevant information necessary for the Council of Ministers to make its decision.

*47. Employees and Former Employees*

1) No receivables, obligations or claims resulting from the overpayment by the Federal Government of Ethiopia of salaries or employment-related allowances, or any part of them shall be written off without the prior approval of the Council of Ministers.

2) Notwithstanding sub-Article (1) of this Article the principle of write-off shall apply to receivables, obligations or claims owing to the Federal Government of Ethiopia by its former employees that are discovered after their employement has ceased and all benefits payable to them have been paid.

*48. Duty to Report*

1) At the end of each month every public body shall prepare a complete analysis of all receivables, obligations and claims and forward a copy of it to the Ministry of Finance. This analysis shall isolate all those receivables, obligations and claims which are considered to be uncollectible and shall be supported by a brief statement of why this determination was made.

2) Subject to directives issued under the authority of Article 53 of the Financial Administration Proclamation, all public bodies shall report all receivables, obligations and claims which are outstanding at the end of every month to the Ministry of Finance and shall report all receivables obligations and claims which are outstanding at the end of every fiscal year in the Public Account for the fiscal year just ended.

፫· ከዚህ በላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከመዝገብ የተሠረዘውን ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ግዴታ እና የይገባኛል ጥያቄ በየወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት የማድረግ እንዲሁም በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ከመዝገብ የተሠረዘውን ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ግዴታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ በዚያው ዓመት ወይም ባለፉት ዓመታት የተፈፀመ መሆኑን በመለየት ሪፖርት ማድረግ አለበት።

፵፱· *መመሪያዎች*

ተሰብሳቢ ሂሳቦችን፣ ግዴታዎችን ወይም የይገባኛል ጥያቄዎችን ወይም የእነዚሁኑ ክፍል ከመዝገብ የመሠረዙ አፈጻጸም የሚመራው ከገንዘብ ሚኒስትር በሚወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

## ክፍል አሥራ አንድ
## የመንግሥት ብድር እና የመንግሥትን ገንዘብ ኢንቬስት ስለማድረግ

፶· የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ

፩· የገንዘብ ሚኒስትሩ ተፈላጊውን የገንዘብ መጠን በተገቢው ጊዜ የመበደርን አጠቃላይ ዓላማ መሠረት ያደረገ እና ወጪን መቀነስን ከተረጋጋ ወጪ ጋር ባመዛዘነ አፈፃፀም መምራት የሚያስችል የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ እንዲመሠረት ማድረግ አለበት።

፪· ብድር ከወለድ ውጪ የሆኑ የተለያዩ የመበደሪያ ሰነዶችን ለመሸጥ የሚደረጉ ወጪዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። የዚህ ዓይነቶቹ ወጪዎች የተለያዩ ኮሚሽኖችን፣ ክፍያዎችን፣ የሬጂስትራሮችን እና የፋይናንስ ወኪሎችን የአስተዳደር ወጪዎች ይጨምራሉ።

፫· ብድር በአጠቃላዩ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ የሆነ ውጤት የሚያስከትሉ በተለይም በገንዘብ ፖሊሲ ወይም በክፍያ ሚዛን ላይ የሚፈጠር አለመረጋጋትን የመሳሰሉ ሁኔታዎችን መከላከል በሚያስችል መንገድ መተዳደር ይኖርበታል።

፬· የአጭር ጊዜ ብድር መንግሥት በባንኮች እና በልውውጥ ገበያ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን የሂሳብ ሚዛን እንዲሁም የገቢ እና የወጪ በጀትን ግምት በሚመለከት አስተማማኝ የሆነ ወቅታዊ መረጃን መሠረት በማድረግ መፈጸም አለበት።

፶፩· ብድር

፩· የገንዘብ ሚኒስትሩ በመንግሥት ዕዳ ረገድ ያሉ መረጃዎችን እና በዕቅድ ተይዞ በነበረው የዕዳ መጠን ላይ የተደረገውን ለውጥ የሚተነትን እንዲሁም በዘመኑ እና በመጪዎቹ ሦስት ዓመታት ይኖራል ተብሎ የሚገመተውን የመንግሥት ዕዳ እና በየዓመቱ ዕዳን ለመክፈል የሚያስፈልገውን ወጪ የሚያሳይ ዓመታዊ የፋይናንስ ዕቅድ በማዘጋጀት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል።

3) In addition, all public bodies shall report all receivables, obligations and claims written off each month to the Ministry of Finance and shall report all receivables, obligations and claims written off in the fiscal year just ended according to whether these write-offs pertained to receivables, obligations and claims of that year or of prior years.

49. *Directives*

The write-off of a receivable, obligation or claim or part of a receivable, obligation or claim shall be done in accordance with directives issued by the Minister of Finance.

## *PART ELEVEN*
## *PUBLIC DEBT AND THE INVESTMENT OF PUBLIC MONEY*

50. *Debt Management Strategy*

1) Debt management strategies shall be developed, by the Minister of Finance based on the overall objective of borrowing appropriate amounts at appropriate times and in a way that will balance minimization of costs with cost stability.

2) Borrowing shall take into account non-interest costs, such as the different marketing costs of various debt instruments; these include the various commissions, fees, and other administrative cost of registrars and fiscal agents.

3) Borrowing shall be managed to avoid any negative impacts on the general economy, such as creating instability in monetary policy or balance of payments.

4) Short-term borrowing shall be based upon reliable, current information on the government's balances in the banking system, exchange market activity, and Budget Estimates of fiscal inflows and outflows.

51. *Borrowing*

1) The Minister of Finance shall prepare an annual Fiscal Plan for the approval of the Council of Ministers that shows background data and analysis of changes in debt from the previous plan, and projections of debt level and annual servicing costs for the present and three upcoming years.

፪· የገንዘብ ሚኒስትሩ የፀደቀውን ዓመታዊ የፋይናንስ ዕቅድ መሠረት በማድረግ የመንግሥትን የፋይናንስ ፍላጐት የሚያሟላ የውሳኔ ሀሣብ በየተወሰነ ጊዜ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል። በዚህ ዓይነት የሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ ገንዘቡ በብድር እና ወይም የዋስትና ሰነዶችን ማውጣትና መሸጥን በመሳሰሉ ዘዴዎች የሚሰበሰብ መሆኑን የሚገልፅ መረጃን መያዝ አለበት።

፶፪· ዋስትና

የገንዘብ ሚኒስትሩ ለግዴታዎች አፈፃፀም ዋስትና ከመሰጠቱ በፊት የሚከተሉት ሁኔታዎች በሚገባ መጣራታቸውን ማረጋገጥ አለበት፣

ሀ) ዋስትናው ያስፈለገበትን ምክንያት እና ከዋስትናው የሚገኘውን ጥቅም፣

ለ) የዋስትናው ግዴታ ተፈጻሚ እንዲሆን ቢደረግ ለዚህ ዓላማ የሚውል የተፈቀደ በጀት መኖሩንና ከየትኛው የበጀት ረዕስ ሊታሰብ እንደሚችል፣ እና

ሐ) በዋስትናው መሠረት ግዴታን የመወጣት ሁኔታ የሚፈጠር ስለመሆኑ የሚኖረውን ግምት እና የሚያስከትለውን ውጤት።

፶፫· ኢንቨስትመንት

፩· በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ የሚገኝ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለክፍያ የማይፈለግ ገንዘብ በዋስትና ሰነዶች ላይ ኢንቬስት ሊደረግ የሚችለው የገንዘብ ሚኒስትሩ ይህ ገንዘብ በእርግጥ ለክፍያ የማይፈለግ ትርፍ ገንዘብ መሆኑን እና የተሻለ ጥቅም ለሚያስገኝ ለሌላ የመንግሥት ዕዳን የማስተዳደር ተግባር እንዲውል ማድረግ የማይቻል መሆኑን ሲያረጋግጥ ይሆናል።

፪· የጥሪት ፈንድ ሊቋቋም የሚችለው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ሲያምንበት ብቻ ይሆናል። የካፒታል ንብረቶችን ለመተኪያ የሚውለው የጥሪት ፈንድ ሊያዝ የሚችለው ለታቀደለት ተግባር እንዲውል ብቻ ነው።

፫· የጥሪት ፈንድ የማቋቋም ተግባር ቢያንስ እንደ ንግድ እንቅስቃሴ ሊያዋጣ መቻሉን ከፋይናንስ ዕቅዱና ከመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ጋር በማያያዝ፣ የፈንዱ መቋቋም የሚያስገኘውን ጥቅም በሚያሳይ ትንታኔ መደገፍ አለበት። ይህ የንግድ ትንታኔ የነበሩትን የኢንቨስትመንት አማራጮች እና የተወሰደው አማራጭ ከሁሉም የተሻለ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት የሚያሳይ መሆን አለበት።

፬· የጥሪት ፈንድ አስተዳደር ራሱን በቻለ የሂሳብ አመዛገብ ሥርዓት እና የጥሪት ፈንዱን እንቅስቃሴ፣ ቀደም ሲል ከቀረበው ሪፖርት በኋላ የተደረገውን ለውጥ እና በታቀደለት ጊዜ ውስጥ ይኖረዋል ተብሎ የሚገመተውን ዋጋ በሚያሳይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚቀርብ ሪፖርት መደገፍ አለበት።

2) The Minister of Finance shall, in accordance with the approved Fiscal Plan, submit for approval of the Council of Ministers periodic proposals to meet the government's financial requirements. These proposals shall contain information on how the money shall be raised such as by loans and/or by the issue or sale of securities.

52. *Guarantee*

The Minister of Finance shall ensure that no guarantee of the performance of an obligation shall be made unless full consideration has been given to:

(a) Why the guarantee is necessary and the benefits that will be gained from it;

(b) The appropriation(s) and budgetary items that would have to be charged if the guarantee is exercised; and

(c) The probability and consequences of the guarantee having to be exercised.

53. *Investment*

1) Money in the Consolidated Fund, that is not immediately required for payments, shall only be invested in securities when the Minister of Finance is satisfied that it is truly surplus to requirements and cannot be put to better use in some other area of public debt management.

2) Sinking funds shall normally only be established where it is considered economically sound by the Council of Ministers. Sinking funds for Capital replacements shall only be reserved for the purpose intended.

3) The creation of a sinking fund shall be supported, as a minimum, by a thorough business case, linked to the Fiscal Plan and the Public Investments Programme, showing why it is beneficial to establish such a fund. This business case shall also show the investment options considered and the reason why the one chosen is best.

4) The management of a sinking fund shall be supported by a system of records and periodic reports to the Council of Ministers on the progress of the sinking fund, any changes made since the previous report, and projections of its expected value by its planned date of maturity.

፭· የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር የሥራ ማስኬጃ ፍላጐትን እና የገንዘብ ፍሰትን እንቅስቃሴ መሠረት በማድረግ የሂሣብ ሚዛን በዝቅተኛ መጠን እንዲቆይ ማድረግ በሚያስችል ሁኔታ መመራት ይኖርበታል።

፶፬· ዕዳን ስለማስተላለፍ

፩· በገንዘብ ሚኒስትሩ ፊርማ የተረጋገጠ ይፋ የሆነ የኢትዮጵያን መንግሥት ስምምነት ካላገኘ በስተቀር የውጭ አበዳሪ የኢትዮጵያን መንግሥት ዕዳ ለማስተላለፍ አይችልም። የገንዘብ ሚኒስትሩ የዚህ ዓይነቱን ሰነድ ከመፈረሙ በፊት ዕዳው የተላለፈው ከዋናው የብድር ስምምነት ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ወይም በተሻሉ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፪· የገንዘብ ሚኒስትሩ ካላፀደቀው በስተቀር የሦስተኛ ወገኖችን የአገር ውስጥ ዕዳ ወይም ከሦስተኛ ወገኖች የአገር ውስጥ ዕዳን የመሰብሰበን መብት ለኢትዮጵያ መንግሥት ማስተላለፍ አይቻልም። በዚህ ዓይነት የሚተላለፍ ዕዳ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑ በገንዘብ ሚኒስትሩ ፊርማ መረጋገጥ አለበት። የገንዘብ ሚኒስትሩ የማስተላለፉን ተግባር ከመቀበሉ በፊት በተገቢው መንገድ የተረጋገጠ ሕጋዊ ሰነድ ሊደርሰው ይገባል።

፶፭· የመንግሥት ባንክ እና የፋይናንስ ወኪል

፩· የገንዘብ ሚኒስትሩ ከፋይናንስ ዕቅድ እና ከብድር አዋጆች የሚመነጩትን የመንግሥትን የገንዘብ ፍላጐቶች በሚመለከት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ይሰጣል።

፪· የገንዘብ ሚኒስትሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመንግሥት የፋይናንስ ወኪልነት ስላደረገው እንቅስቃሴ ወርሀዊ ሪፖርት እንዲያቀርብለት በመጠየቅ የባንኩን አፈፃፀም መከታተል አለበት።

፶፮· መዝገቦች እና ሂሳቦች

የገንዘብ ሚኒስትሩ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፵፭ መሠረት የመንግሥት ዕዳ አስተዳደርን የሚመለከት የመዝገብ እና የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት እንዲመሠረት ያደርጋል። ይህም ሥርዓት የሚከተሉትን የሚጨምር ይሆናል፣

ሀ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት በብድር እንዲወሰድ የተፈቀደውን ማናቸውንም ገንዘብ፣

ለ) በብድር የተወሰደውን ማናቸውንም ገንዘብ የሚያሳይ መግለጫ፣

ሐ) በብድር ከተወሰደው ገንዘብ ውስጥ የተከፈለውን ዋና ዕዳ ወይም ወለድ፣

መ) ለኢንቨስትመንት የዋለውን ማናቸውንም ገንዘብ መግለጫ፣

ሠ) ከኢንቨስትመንት የተገኘውን ገቢ እንዲሁም እነዚህን ኢንቨስትመንቶች ለመያዝ፣ ለማስተዳደር እና ለማስለቀቅ የተከፈለውን ገንዘብ፣

ረ) የተፈቀዱ ዋስትናዎችን የሚያሳይ መግለጫ፣

ሰ) ዋስትና ለተገባለት ግዴታ ከተጠቃለለው ፈንድ የተፈፀመውን ክፍያ ክፍያውን መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት ጭምር።

5) Cash shall be managed to keep balances at minimum levels, given operational needs and the variability of cash flows.

*54. Assignment of Debts*

1) No assignment of debts of the Government of Ethiopia shall be made by a foreign lender without the formal agreement of the Government of Ethiopia evidenced by the signature of the Minister of Finance. Before signing the Minister must establish that the assignment is under the same, or better terms and conditions for the Government of Ethiopia than the original debt arrangement.

2) No assignment of the domestic debts of third parties or the right to collect the domestic debts of third parties shall be made to the government without the approval of the Minister of Finance. Such assignments must have the signed acknowledgement of the assignment by the Minister of Finance. Before acknowledging the assignment, the Minister of Finance shall be provided with the properly authenticated legal documents.

*55. Government's Banker and Fiscal Agent*

1) The Minister of Finance shall instruct the National Bank of Ethiopia on the government's requirements arising from the Fiscal Plan and Borrowing Proclamations.

2) The Minister of Finance shall monitor the performance of the National Bank of Ethiopia by requiring it to provide monthly reports on its activities as the government's fiscal agent.

*56. Books and Records*

The Minister of Finance shall cause to be maintained a system of books and records on its public debt management in accordance with *Article 45* of the Proclamation. In addition, this system will:

(a) Show all money authorized by the Council of Ministers to be borrowed,

(b) Contain a description of and record of all money so borrowed;

(c) Show all money paid in respect of the principal of or interest of all money so borrowed;

(d) Contain a description of and record of all money invested and;

(e) Show all money earned from this money so invested, as well as amounts paid for the acquisition, administration, and redemption of these investments;

(f) Contain a description and record of all guarantees authorized and;

(g) Show all payments out of the Consolidated Fund against such guarantees, including the reasons why such payments were necessary;

፶፯· ሪፖርት

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ወርሀዊ የገንዘብ ፍላጎታቸውን ግምት እና የየወሩን የገንዘብ አጠቃቀም ሪፖርት በዚህ ደንብ መሠረት የገንዘብ ሚኒስትሩ የሚያወጣውን መመሪያ በመከተል ማቅረብ አለባቸው።

## ክፍል አሥራ ሁለት
## የመንግሥት ንብረት

፶፰· መርህ

የመንግሥትን ንብረት በንብረትነት የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የጥገና፣ የጥበቃ እና የማስወገድ ተግባር በአነስተኛ በጀት በመጠቀም ውጤታማ፣ ቀልጣፋ እና ኤኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ መፈጸሙ መረጋገጥ አለበት።

፶፱. ንብረትን ስለመያዝ

፩. ማናቸውንም የመንግሥት ንብረት በባለቤትነት የመያዝ ብቸኛ ዓላማ ፡ የፀደቁትን የመሥሪያ ቤቱን ፕሮግራሞች ለማስፈፀም እና አገልግሎቱን በማፋጠን በተቻለ መጠን ውጤታማና ብቁ ለማድረግ መሆን አለበት።

፪. የገንዘብ ሚኒስቴር በማናቸውም የፌዴራሉ መንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር ያልሆኑትን የፌዴራሉን መንግሥት ንብረቶች በመንግሥት ንብረትነት ይይዛል።

፷. አጠቃቀምና ጥገና

፩. የማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት በተቻለ መጠን የመሥሪያ ቤቱን ኃላፊነት ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ አለበት።

፪. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የመንግሥት ንብረት በተቻለ መጠን ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢ የጥገና ሥርዓት ማቋቋም አለበት።

፷፩. የመንግሥት ንብረት አስተዳደር

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግሥት ንብረት ለማስተዳደር የሕይወት ዘመን ሥርዓትን ይከተላል።

፪. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግሥት ንብረትን ከተያዘበት ከአገልግሎት ውጪ እስከሆነበት ቀን ድረስ ቀኑን ፡ ዝርዝር መግለጫውን ፡ ብዛቱን እና ያስከተለውን ወጪ የሚያሳይ ዝርዝር መመዝገቡን ማረጋገጥ አለበት።

፫· የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመሥሪያ ቤቱን ማናቸውንም ቋሚ ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት በመጀመሪያ ደረጃ ንብረቱን እንዲገለገሉበት ኃላፊነት ለተሰጣቸው ኃላፊዎች መሰጠቱንና በዋናው ማዕከላዊ መዝገብ የጠባቂዎቹ ዝርዝርና በእነርሱ ጥበቃ ስር ያሉት ቋሚ ንብረቶች የሚገኙበት ቦታ መስፈሩን ማረጋገጥ አለበት።

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የማይውሉ አላቂ ዕቃዎች በዕቃ ዝርዝር መዝገብ ውስጥ መካተታቸውንና ለጥበቃቸው ኃላፊ መመደቡን ማረጋገጥ አለበት።

፭· ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ እየተቆጠረ ከዕቃ ዝርዝር መዝገብ ጋር በመመሳከር መረጋገጥ አለበት።

57. *Reporting Requirements*

The Heads of public bodies shall submit monthly forecasts of cash requirements and monthly reports of financial usage in accordance with directives issued by the Minister of Finance under these Regulations.

## *PART TWELVE*
## *PUBLIC PROPERTY*

58. *Principle*

The public property shall be managed to ensure economy, efficiency and effectiveness in its acquisition, use, maintenance, protection and disposal within budgetary constraints.

59. *Acquisition*

1) All acquisitions of public property shall be for the sole purpose of facilitating the delivery and maintenance of approved programmes as efficiently and effectively as possible.
2) The Ministry of Finance shall account for and administer property of the Federal Government which is not administered or used by any other public body.

60. *Use and Maintenance*

1) Heads of Public Bodies shall ensure that all public property is used as productively as possible in carrying out the responsibilities of their public bodies.
2) Heads of Public Bodies shall establish a proper maintenance system for all public property to ensure that it will operate as economically and effectively as possible in accordance with the directives of the Minister of Finance.

61. *Management of Public Property*

1) The Heads of public bodies shall adopt a life-time approach to the Management of public property.
2) The Heads of public bodies shall ensure that items of public property are recorded as to date, description, quantity and cost from acquisition to the end of their life-time.
3) The Heads of public bodies shall ensure that the custodial responsibility for each fixed asset acquired is assigned to the primarily responsible for its use and that there is a central record of the names of the custodians and the locations of the fixed assets assigned to them.
4) The Heads of public bodies shall ensure that supplies, not acquired for immediate consumption, shall form part of supply inventories and that custodial responsibility be assigned for such inventories.
5) All inventories of public property shall be physically verified against records atleast annually.

፮. የመንግሥትን ንብረት ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን ሳይቻል ሲቀር ግምቱ የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

፯. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የማናቸውም የአላቂ ዕቃ ዝርዝርና የቋሚ ንብረት መግለጫና ዋጋ በመንግሥት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ መጠቃለሉን ማረጋገጥ አለበት።

፰. የዋጋ እና የወጪ አተማመን ሥርዓት የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፷፪. <u>መጠበቅና መንከባከብ</u>

ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ እና ሠራተኞች የመንግሥትን ንብረት የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት አለባቸው።

፷፫. <u>ማስወገድ</u>

፩. የመንግሥት ንብረት የሚወገደው የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

፪. የተወገደ የመንግሥት ንብረት መግለጫና ንብረቱን በማስወገድ የተገኘው ገንዘብ መጠን በመንግሥት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ መጠቃለል አለበት።

፷፬. <u>መሠረዝ</u>

፩. የመንግሥት ንብረት ለሚገኝበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የማይጠቅም ምንም ዋጋ የማያወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሠረዛል።

፪. የመንግሥት ንብረት ሲበላሽ፣ ከጥቅም ውጪ ሲሆን፣ ሲሰረቅ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሣሣይ ምክንያት ሲጎድል ወይም ሲጠፋ ከንብረት መዝገብ ይሠረዛል።

፫. ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ሲሰረዝ መግለጫውና የገንዘቡ መጠን የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በመንግሥት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ ተጠቃልሎ መታየት አለበት።

፷፭. <u>ገቢዎች</u>

፩. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከመንግሥት ንብረት ገቢ የሚሰበስበው የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መሆን አለበት።

፪. ገቢውን ያገኘው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በገቢው በመጠቀም ካልተፈቀደለት በቀር በመንግሥት ንብረት በመገልገል ወይም የመንግሥትን ንብረት በማስወገድ የተገኘ ማናቸውም ገቢ ፡ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት።

## ክፍል አሥራ ሶስት
## <u>ግዥዎችና ውሎች</u>

፷፮. <u>መርህ</u>

፩. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለሚፈጽማቸው ማናቸውም የግዥ ውሎች የሚከፍለው የመንግሥት ገንዘብ ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ ማግኘቱን ማረጋገጥ አለበት።

፪. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የዕቃው ጥራትና ዋጋ ተመሣሣይ ሲሆንና በኢትዮጵያ የተመረተው ምርት ከውጪው አገር ባነሰ ወይም በተመሳሳይ ጊዜ ሊቀርብ የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም ማናቸውንም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወሰንን ሌላ ሁኔታ ሲያሟላ ከውጭ አገር ምርት የአገር ውስጥን ምርት መምረጥ አለበት።

6) Where the actual cost of public property is not determinable, its cost shall be estimated in accordance with directives from the Minister of Finance.

7) The Heads of public bodies shall ensure that the value of all inventories of supplies and the description and cost of fixed assets shall be included in the Public Accounts in accordance with directves of the Minister of Finance.

8) Valuation and Costing of public property shall be determined by the directives of the Minister of Finance.

62. *Protection and Preservation*

The Heads and all employees of public bodies are responsible for the protection and preservation of public property.

63. *Disposal*

1) The disposal of public property shall be in accordance with directives of the Minister of Finance.

2) The description and amount received from all public property disposed of shall be included in the Public Accounts.

64. *Deletion*

1) Where public property is considered to be of no use in the public body or elsewhere, and has no scrap value, it shall be deleted in accordance with the directives of the Minister of Finance.

2) Deletion of public property shall be recorded when losses take place from inventory shortages, destruction, theft or any other reason.

3) The description and amounts of all public property deleted shall be included in the Public Accounts in accordance with the directives of the Minister of Finance.

65. *Revenues*

1) The raising of any revenues on public property by public bodies shall be in accordance with directives of the Minister of Finance.

2) All revenues from the use or disposal of public property shall be deposited in the Consolidated Fund unless a public body has the authority to retain and expend these revenues.

## *PART THIRTEEN*
## *PROCUREMENT-CONTRACTS*

66. *Principle*

1) All public bodies shall ensure that they obtain the best Value for the public money they spend in awarding all their procurement contracts.

2) Public bodies shall purchase goods produced in Ethiopia in preference to goods produced abroad where the price and quality are similar and where the goods produced in Ethiopia are to be delivered within similar time as or a shorter time than the goods produced abroad, or any other considerations as determined by the Council of Peoples' Representatives.

፷፯. የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር

፩. የገንዘብ ሚኒስትር አግባብ ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር በዚህ አንቀጽ ለሌሎች መሥሪያ ቤቶች የተሰጠውን ሳይጨምር ማናቸውንም የአገር ውስጥ ግዢዎችን በሚመለከት የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ያዘጋጃል፣ ይይዛል፣

፪. የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር የኮንስትራክሽን ሥራ ውሎችን በተመለከተ የአቅራቢዎችን ዝርዝር ያዘጋጃል፣ ይይዛል።

፫. የገንዘብ ሚኒስትር እንዲሁም የኮንስትራክሽን ሥራዎችን በተመለከተ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመግባት ምን ምን መመዘኛዎች መሟላት እንዳለባቸው የሚያሳይ መመሪያ ያወጣሉ።

፬. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር የተሽከርካሪዎች ግዢን በተመለከተ የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ያዘጋጃል፣ ይይዛል።

፭. የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን ዝርዝር ያዘጋጃል፣ ይይዛል።

፮. የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር የሚያዘጋጁ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዝርዝሩ ውስጥ የሚታቀፉትንና ከዝርዝሩ የሚወጡትን በሚመለከት በየጊዜው ማሻሻያዎችን ማድረግ አለባቸው።

፷፰. ጨረታ

፩. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ማናቸውንም ውል ከመፈፀሙ በፊት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተገለፀው መሠረት ጨረታ ማውጣት አለበት።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ፤ ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከዚህ በታች ከተመለከቱት ሁኔታዎች አንዱ ሲሟላ ጨረታ ማውጣት ሳያስፈልግ ውል መፈጸም ይችላል፣

ሀ) የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ (ለሌላ ውክልና መስጠት አይቻልም) በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሣ ቢዘገይ በመሥሪያ ቤቱ ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥርና በመሥሪያ ቤቱ የሥራ አፈጻጸም ላይ ጉዳትን የሚያስከትል መሆኑን በማመን በፅሑፍ ሲያረጋግጥ፣

ለ) የሚደረገው ወጪ ግምት ገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን፣

ሐ) ከሥራው ዐባይ አንፃር ሲታይ ጨረታ ማውጣቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ፍላጎት ሳይሆን ሲቀር፣

መ) ውሉን መፈጸም የሚችል አንድ የሥራ ተቋራጭ ብቻ ሲሆን።

፫. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጨረታ የሚያወጣው፣

ሀ) የተለመደውን ተቀባይነት ያለውን አሠራር መሠረት በማድረግ በመገናኛ ብዙሀን የጨረታ ጥሪ በማስተላለፍ ፣ ወይም

ለ) ከዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የታቀደውን ሥራ እንዲያከናውኑ የተወሰኑ አቅራቢዎችን ለጨረታ በመጋበዝ ፣ ወይም

ሐ) ዕቃ አቅራቢዎች ያላቸውን ብቃትና ችሎታ በማየት ብቻ በማወዳደር ይሆናል።

*67. Suppliers List*

1) The Minister of Finance in consultation with an appropriate public body shall establish and maintain a suppliers list for all local purchases, except in so far as is provided to other public bodies under this Article.
2) In the case of construction contracts, a suppliers list shall be established and maintained by the Minister of Works and Urban Development.
3) The Minister of Finance shall issue directives listing the criteria for the inclusion of contractors on suppliers lists and the Minister of Works and Urban Development shall do likewise for construction contractors.
4) Minister of Communication and Transport shall prepare and maintain Suppliers List for the Purchase of Vehicles.
5) Minister of Economic Development and Cooperation shall prepare and maintain suppliers list for consultancy services.
6) Public bodies empowered to prepare and maintain Suppliers List shall from time to time include into or delete from the Suppliers List.

*68. Bids*

1) Before entering into any contract, all public bodies shall solicit bids for such contracts in the manner prescribed by sub-article 3 of this Article.
2) Notwithstanding sub Article (1) of this Article; a public body may enter into a contract without soliciting bids where any one of the following conditions apply:
   (a) The Head of the public body had determined (this shall not be delegated by him or her) and has documented that the need is one of pressing emergency in which delay would create serious problems and thereforebe injurious to the preformance of that public body;
   (b) the estimated expenditure does not exceed the amount to be determined by directives of the Minister of Finance;
   (c) the nature of the work is such that it would not be in the interests of the Government of Ethiopia to solicit bids;
   (d) only one contractor is capable of performing the contract.
3) All public bodies shall solicit bids by:
   (a) giving public notice, in accordance with generally accepted practices, of a call for bids respecting a proposed contract, or
   (b) inviting bids on a proposed contract from suppliers on a suppliers' list, or
   (c) short-listing suppliers by the process of prequalification.

፬. የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ በተለየ ሁኔታ እንዲታይ ካልተደረገ በስተቀር የውጪ ግዢዎች በዓለም አቀፍ የጨረታ አፈጻጸም ሥርዓት መሠረት ይከናወናሉ።

፭. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚያወጡት ጨረታ መሳተፍ የሚችሉት በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮች ብቻ ናቸው።

፮. የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ግዢ የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር በሚያወጣው ዝርዝር (ስፔሲፊኬሽን) መሠረት ይፈጸማል።

፷፱. የጨረታ ማስከበሪያ

፩. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሥራ ተቋራጮች ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የጨረታ ማስከበሪያ እንዲያስይዙ መጠየቅ አለበት።

፪. የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለጨረታ ማስከበሪያ ጥሬ ገንዘብ ፣ ቼክ ወይም የጨረታ ማስፈጸሚያ ቦንድ ሊቀበል ይችላል።

፫. የመንግሥት መሥሪያ ቤት በዋስትና ሰነዱ ላይ የተመለከቱት ግዴታዎች እስኪፈጸሙ ድረስ የጨረታ ማስከበሪያ ውን መያዝ አለበት ።

፬. ለጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ የሚቻለው የገንዘብ መጠን የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፭. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተቀበለውን ማናቸውም የጨረታ ማስከበሪያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) እና (፯) መሠረት እስኪመለስ ድረስ መያዝ አለበት።

፮. ጨረታው ተቀባይነት ሲያገኝና የውል ማስከበሪያ እንዲሰጥ ሲጠየቅ፣

ሀ) የውል ማስከበሪያው እስኪሰጥ ድረስ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የጨረታ ማስከበሪያውን መያዝ እና

ለ) የጨረታ ማስከበሪያው የውል ማስከሪያው አካል ካልሆነ በስተቀር የውል ማስከበሪያው እንደተገኘ ለሥራ ተቋራጩ መመለስ አለበት።

፯. ተጫራቹ በጨረታው ሳያሸንፍ ሲቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተቀበለውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለሥራ ተቋራጩ ይመልሳል።

፸. የውል ማስከበሪያ

፩. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሥራ ተቋራጮች ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የውል ማስከበሪያ እንዲሰጡ መጠየቅ አለበት።

፪. የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጥሬ ገንዘብ ፣ ቼክ፣ የማስፈጸሚያ ቦንድ፣ የሚተላለፍና የማይተላለፍ የገንዘብ ሰነድ በውል ማስከበሪያነት ሊቀበል ይችላል።

፫. የመንግሥት መሥሪያ ቤት በውል ማስከበሪያነት ጥሬ ገንዘብ ወይም ቼክ የተቀበለ እንደሆነ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፷፱ (፮) (ለ) መሠረት የጨረታ ማስከበሪያውን የያዘ እንደሆነ ይህንኑ ወዲያውኑ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ማስቀመጥ አለበት።

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚተላለፍ የዋስትና ተቀማጭ ሰነድ በውል ማስከበሪያነት የተቀበለ ሲሆን፣

ሀ) የውል ማስከበሪያውን ካዝና ማስቀመጥ ፣ ወይም

ለ) የውል ማስከበሪያውን ገንዘብ ሚኒስትር እንዲያስቀምጥ ወዲያውኑ መላክ አለበት።

4) Foreign purchases will be made by means of International Competitive Bidding unless there are exceptions provided in directives of the Minister of Finance.

5) Only contractors in the approved Suppliers' list may bid on contracts to be awarded by public bodies.

6) All Purchases of Vehicles shall be made in accordance with specifications of the Ministry of Transport and Communication.

*69. Bid Security*

1) All public bodies shall require contractors to give the Federal Government of Ethiopia bid security.

2) A public body may accept cash, cheque or a bid bond as bid security.

3) A public body shall hold any bid security that is received by it until the terms of the security are fulfilled.

4) The amounts of any bid security shall be established by directives issued by the Minister of Finance.

5) A public body shall hold any bid security received by it until it can be disposed of in accordance with sub-Articles (6) and (7) of this Article.

6) Where a bid is accepted and contract security is required to be provided,
   (a) the public body shall continue to hold the bid security until the contract security is provided; and
   (b) when the contract security is provided, the public body shall return the bid security to the contractor from whom it was received unless it forms part of the contract security, in which case it shall be retained as contract security.

7) Where a bid is rejected, the public body shall return the bid security to the contractor from whom it was received.

*70. Contract Security*

1) All public bodies shall require contractors to give the Federal Government of Ethiopia contract security.

2) A public body may accept as contract security cash, a cheque, a performance bond, a negotiable or a non negotiable security.

3) Where cash or a cheque is received by a public body as contract security or is retained by a public body in accordance with Article 69(6)(b) of these Regulations, the public body shall immediately deposit the cash or cheque in the Consolidated Fund.

4) Where a negotiable security deposit is received, the public body shall:
   (a) hold the contract security in safe keeping; or
   (b) immediately forward the contract security to the Minister of Finance for safekeeping.

፭. የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለውሉ ማስከበሪያ የተቀበለው የሚተላለፍ የዋስትና ተቀማጭ ሰነድ ሲሆንና ውሉ፣
  ሀ) በተሟላ ሁኔታ ሲፈጸም ወይም፣
  ለ) ሥራ ተቋራጩ የፈፀመው ምንም ጥፋት ሳይኖር ውሉ ሲቋረጥ እና የኢትዮጵያ የፌዴራላዊ መንግሥት በውሉ ምክንያት ወይም ከውሉ ጋር በተያያዘ በሥራ ተቋራጩ ላይ የሚያቀርበው ምንም የይገባኛል ጥያቄ ሳይኖር ሲቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤት የዋስትና ተቀማጩን ለሥራ ተቋራጩ መመለስ አለበት።

፸፩. <u>ብድር እና እርዳታ</u>

የፋይናንስ ምንጫቸው ከውጭ አገር ብድር እና/ወይም ዕርዳታ የሆነ ውሎች በባለሁለት ወይም በባለብዙ ወገን ስምምነት ይገዛሉ።

፸፪. <u>በየደረጃው የሚደረግ ክፍያ</u>

፩. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለውሉ አፈጻጸም ቀልጣፋነትና ውጤታማነት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ክፍያው በየደረጃው እንዲሆን የሚፈቅድ ውል መዋዋል ይችላል።

፪. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሥራ ተቋራጩ በውሉ መሠረት ግዴታው መፈጸሙንና በሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ፈቃድ ከሥራ ተቋራጩ ጋር የሚሰሩት ማናቸውም ንዑስ የሥራ ተቋራጮች ተገቢውን ክፍያ ማግኘታቸው እስኪረጋገጥ ድረስ በየደረጃው እንዲከፈል ከተያዘው ውስጥ የተወሰነውን ገንዘብ መቀነስ ወይም ይዞ መቆየት አለበት።

፫. ተይዞ የሚቆየው ገንዘብ መጠንና ለምን ያህል ጊዜ ሊያዝ እንደሚችል በገንዘብ ሚኒስትር በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

፸፫. <u>ውሎች የሚመሩባቸው ደንቦች</u>

የዚህ ደንብ ልዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የመንግሥት ግዥ አፈጻጸም በፍትሐብሔር ሕግ የአስተዳደር ክፍል መሥሪያ ቤቶች ስለሚያደርጉዋቸው ውሎች በተደነገገው መሠረት የሚመራ ይሆናል።

## <u>ክፍል አሥራ አራት</u>
## <u>የፌዴራል/ክልል የፋይናንስ ግንኙነቶች</u>

፸፬. <u>የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት</u>

፩. የክልል መንግሥት የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ከፌዴራል መንግሥት ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።

፪. ሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲሟላ የሚጠይቀው የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መጠበቅ አለበት ።

፫. የክልል መንግሥታት የፌዴራል እና የክልሎችን የፋይናንስ ግንኙነቶች ለማቀላጠፍ የሚያስችል የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ለማቋቋም እና ለመያዝ እንዲችሉ የገንዘብ ሚኒስትር ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል ።

5) Where a negotiable security deposit has been received by a public body in respect of a contract and the contract has been:
   (a) satisfactorily performed, or
   (b) terminated for a reason that is not attributable to any fault of the contractor,
   and the Federal Government of Ethiopia has no claim against the contractor arising out of the contract or relating in any manner to the contract, the public body shall return that security deposit to the contractor.

71. *Loan and Aid*

Contracts which are financed by foreign loans and/or aid shall be governed by the terms of the bilateral or multilateral agreement.

72. *Progress Payment*

1) Any public body may enter into a contract that provides for the making of progress payments where it is deemed necessary for the most efficient and effective execution of the contract.
2) A public body shall retain or hold back a portion of the progress billings called for under the terms of every contract until the public body is satisfied that the contract has been completed and that all nominated subcontractors who have been approved by the public body concerned have been paid by the contractor.
3) The amount retained and the duration of the retention shall be stipulated in directives issued by the Minister of Finance.

73. *Provisions applicable to Contracts*

Without limiting the special provisions of these Regulations, government procurement shall be governed by the Provisions of Administrative Contracts under the Civil Code of Ethiopia

## *PART FOURTEEN*
## *FEDERAL/STATE FINANCIAL RELATIONS*

74. *Financial Reporting Systems*

1) The financial reporting systems of State Governments shall correspond with those of the Federal Government.
2) The financial reporting requirements of the Council of Ministers shall be observed by the Federal and State Governments.
3) The Minister of Finance shall provide the necessary guidance and support to State Governments to enable them to establish and maintain financial reporting systems that will facilitate Federal-State financial relations.

፬. የክልል መንግሥታት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚጠይቀውን በማሟላት እና የገንዘብ ሚኒስትር ያወጣውን ፎርም በመከተል በየወሩ ፣ በየሩብ ዓመቱ ፣ በየግማሽ ዓመቱ እና በየዓመቱ የፋይናንስ ሪፖርት ለገንዘብ ሚኒስትር ያቀርባሉ። እነዚህም ሪፖርቶች የክልሎችን ገቢዎችና ወጪዎች በምንጫቸውና በሂሣብ መለያ ቁጥሮች በመለየት ፣ ያላቸውን ጥሬ ገንዘብ ፣ ያልተከፈለውን ዕዳ መጠንና የሥራ አፈጻጸማቸውን የድጋፍ በጀት ከጠየቁበት ዓላማ ጋር በማነፃፀር ማሣየት አለባቸው ።

፭. የገንዘብ ሚኒስትር በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የክልል መንግሥታት ያቀረቡትን ዝርዝር በመከተል የተጠቃለለና የተነጻጸረ ወርሃዊ የሩብ ዓመት ፣ የግማሽ ዓመትና ዓመታዊ የክልሎች የፋይናንስ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል።

፮. የገንዘብ ሚኒስትር በክልሎችና በፌዴራል መንግሥት መካከል የተደረጉ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን የሚያሣይ የተሟላ መዝገብ ይይዛል ።

፸፭. የአገር ውስጥ ብድር

፩. የክልል መንግሥታት የፋይናንስ ፍላጎቶች ከፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ዕቅድና በጀት ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው። በሁለቱ መንግሥታት ደረጃ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፋይናንስ ድርጅቶች የተቀራረበ የሥራ ግንኙነት ኖሮዋቸው በበጀት ዓመቱ ውስጥ አጠቃላይ የብድር ወጪዎችን ለመቀነስና ብሔራዊ ኢኮኖሚውን በሚጠቅም መሠረታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው ።

፪. ገንዘብ ሚኒስትር ለክልል መንግሥታት በብሔራዊ ባንክና በሌሎች ድርጅቶች የሚደረገውን የብድር ክፍያ አፈጻጸም ይከታተላል ፣ ከክልል መንግሥታት በየጊዜው ከሚቀበለው የፋይናንስ ሪፖርት ጋር ያስታርቃል ።

፸፮. የታክስ ውህደት

፩. በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት ደረጃ አዳዲስ ታክሶች በሚጣሉበት ወይም ነባር ታክሶች በሚለወጡበት ጊዜ የታክስ መሠረቱ ተመሳሳይ እና የተዋሃደ መሆኑን ለማረጋገጥ በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል ምክክር መደረግ አለበት።

፪. የገንዘብ ሚኒስትር የክልል መንግሥታት የሚጥሉት ታክስ መሠረቱ የፌዴራል መንግሥት ከሚጥለው ጋር ተመሳሳይ እና የተዋሃደ እንዲሆን ለማድረግ የጥናት እና የአስተዳደር ድጋፍ ይሰጣል።

፸፯. የበጀት ድጋፍ እና የውጭ ምንዛሪ

፩. የፌዴራል መንግሥቱ የክልል መንግሥታት በጀታቸውን በጊዜ ለማዘጋጀት እንዲችሉ የሚሰጣቸውን የድጎማ በጀት ጣሪያ በወቅቱ ያሳውቃል።

፪. የክልል መንግሥታት በጀታቸውን ከማጽደቃቸው በፊት የድጋፍ በጀት ጥያቄያቸውን ለገንዘብ ሚኒስትርና ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ያቀርባሉ።

፫. የክልል መንግሥታት የውጭ ምንዛሪ ፍላጎታቸውን ለገንዘብ ሚኒስቴር ያሳውቃሉ።

፸፰. ቅጾችና የጊዜ ገደብ

የገንዘብ ሚኒስትር የክልል መንግሥታት ፣

ሀ) የድጋፍ በጀት ፣ ጥያቄያቸውን ፣ የገቢ ግምታቸውን ጭምር

ለ) የአገር ውስጥ ብድርን እና

ሐ)የውጭ ምንዛሪ ፍላጎታቸውን

የሚያቀርቡበትን የጊዜ ገደብ እና ቅጽ ያዘጋጃል።

4) The State Governmets shall provide monthly, quarterly, semi-annual and annual financial reports to the Minister of Finance that follow the formats developed by the Minister of Finance in accordance with the requirements of Council of Ministers. These reports shall show details of their receipts and disbursements by revenue and expenditure source codes; their cash balances and levels of outstanding debt; and their performance against the objectives stated in their subsidy requests.

5) The Minister of Finance shall prepare consolidated and comparative monthly, quarterly, semi-annual and annual financial reports for State Governments, in accordance with the details submitted by those governments as described in sub-Article (4) of this Article and submit them to the Council of Ministers.

6) Complete records on the financial transactions between the Federal and State Governments shall be maintained by the Minister of Finance.

75. *Domestic Borrowing*

1) The financial requirements of the State Governments shall be closely aligned with the Federal Government's fiscal plan and budget and both levels of Government shall ensure that their respective financial organizations maintain close working relations during the course of the fiscal year to minimize overall borrowing costs and to act in the best interests of the national economy.

2) The Minister of Finance shall monitor the disbursements of the National Bank of Ethiopia and any other entities against the borrowings of State Governments and reconcile these with the periodic financial reports it receives from the State Governments.

76. *Tax Harmonization*

1) Consultations between Federal and State Governments shall take place on all new or changed taxes at both levels of government to ensure that the tax bases are harmonized and standardized.

2) The Minister of Finance shall provide, as required, research and administrative support to State Governments to facilitate the harmonization and standardization of their tax bases with those of the Federal Government.

77. *Subsidy and Foreign Currency*

1) The Federal Government shall advise the State Governments of their budget subsidy ceillings in time for them to prepare their regional budgets.

2) Before the approval of the budget, State Governments shall submit to the Ministers of Finance and Economic Development and Cooperation their subsidy requests.

3) State Governments shall submit their foreign currency requirements to the Ministry of Finance.

78. *Formats and Deadlines*

The Minister of Finance shall establish the format and deadlines for the submissions by State Governments of their:

(a) Subsidy requests, including their revenue forecasts;
(b) internal borrowings; and
(c) foreign currency requirements.

፸፱. የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት

የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል የተደረጉትን የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች ፣ የክልል መንግሥታትን የድጋፍ በጀት አፈጻጸም ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር በማነጻጸር እና የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን የፋይናንስ ሁኔታ የሚያሳይ የበጀት ዓመቱን የመጨረሻ ሪፖርት በተጠቃለለና በተነጻጸረ መልኩ የሚይዝ መሆን አለበት።

፹. ኦዲት

፩. የገንዘብ ሚኒስቴር የክልል መንግሥታት ከፌዴራል መንግሥት ያገኙትን የድጋፍ በጀት አጠቃቀም በተመለከተ አስፈላጊውን የኦዲት ሥራ ለማካሄድ እንዲችል የክልል መንግሥታትን ሂሣብ ለማየት ይችላል።

፪. የጠቅላይ ኦዲተር እንደ አንድ መደበኛ የኦዲት ፕሮግራም የፌዴራል መንግሥት ከክልል መንግሥታት ጋር ያደረገውን የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚመለከቱ መዛግብትን ይመረምራል።

## ክፍል አሥራ አምስት
## የመንግሥት ገንዘብና ንብረት ስለመጥፋት

፹፩. ምርመራ ስለማካሄድ

፩. የመንግሥት ንብረትና ገንዘብ ስለመጥፋቱ ወይም ስለመጉደሉ በየትኛውም መልኩ በቀረበው ሪፖርት ላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ሙሉ ትብብር ኖሮ የተሟላ ምርመራ መደረግ አለበት።

፪. የወንጀል ተግባርን ከማይጨምሩ አነስተኛ ከሥራ ጋር የተያያዙ ጥፋቶች በስተቀር ጥፋት እንዳለ ጥርጣሬ ሲኖር ለፖሊስ ሪፖርት መደረግ አለበት።

፫. በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚካሄደው የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ ጥፋት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ ላይ የተወሰነ ይሆናል።

፬. ጉዳዩ የሚመለከተው የመምሪያ ኃላፊ የፖሊስ ምርመራ የማይፈልጉ በሠራተኞች የተፈፀሙ ጉድለቶች ላይ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የመሥሪያ ቤቱን የሕግ ክፍል ስለጉዳዩ አሳሳቢነት አስተያየት ሊጠይቅ ይችላል።

፹፪. ሪፖርት ስለማቅረብ

፩. ማናቸውም የመንግሥት ሠራተኛ ጥፋት መፈፀሙን ሲደርስበት ወይም ሲጠረጥር ወዲያውኑ ለክፍሉ ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ አለበት። ኃላፊው የቀረበለት ሪፖርት ወዲያውኑ ለአስተዳደር መምሪያ በጽሁፍ ሪፖርት መደረጉን እንዲሁም የመ/ቤቱ የሕግ እና የኦዲት መምሪያዎች የሪፖርቱ ግልባጭ የደረሳቸው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። የአስተዳደር መምሪያው ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊና ለገንዘብ ሚኒስቴር የሪፖርቱን ግልባጭ ይልካል።

፪. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጥፋት መፈፀሙን ሲያውቁ ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ለሠራተኞቹ ማሳወቅ አለበት።

፹፫. የፍትሐብሔር እርምጃ

፩. ማናቸውንም የገንዘብና የንብረት ጉድለት ለማስመለስ የሚያስችል እርምጃ የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መወሰድ አለበት።

፪. የገንዘብ ሚኒስትር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ክሱን እንዲያቆም በተለይ ካልፈቀደ በስተቀር የመንግሥት ሠራተኛ ተጠያቂ የሆነበትን ያጎደለውን ንብረት ወይም ገንዘብ መመለስ አለበት።

*79. Public Accounts*

The Public Accounts shall contain details of the financial transactions between Federal and State Governments, performance against the financial plans of State Governments vis-a-vis their budget subsidies, and fiscal year-end reports on the financial status of the Federal and State Governments on a consolidated and comparative basis.

*80. Audit*

1) The Ministry of Finance shall have access to the accounts of the State Governments necessary for it to conduct audits of their use of budgetary subsidies received from the Federal Government.
2) The Auditor General, as part of his or her normal audit programme, should audit the Federal Government's records of its financial transactions with State Governments.

## *PART FIFTEEN*
## *LOSSES OF PUBLIC MONEY AND PUBLIC PROPERTY*

*81. Investigation*

1) All losses of public money and public property, however they are reported, require full investigation with the complete cooperation of all the employees of the public body.
2) Suspected losses, with the exception of certain minor, employment-related incidents which do not involve criminal activity, must be reported to the police.
3) Any preliminary examination undertaken by a public body shall be limited to ascertaining whether there is a possible basis to an allegation.
4) The responsible department head may refer suspected losses involving employees, that do not require an immediate response by the police, to the public body's legal branch for an opinion on the seriousness of the incident before further action is taken.

*82. Reporting*

1) Every employee who discovers or suspects that a loss has occurred shall report it immediately to the head of his or her department. The latter is responsible for ensuring that all losses which are reported to him or her are promptly reported in writing to the administration department of the public body with copies of the report to its legal and internal audit departments. In addition the administration department will forward a copy of this report to the Head of the Public Body and the Ministry of Finance.
2) All public bodies must ensure that all their employees are aware of their responsibility to report all losses of which they have knowledge.

*83. Civil action*

1) Action must be undertaken in accordance with directives issued by the Minister of Finance to recover all losses.
2) When an employee is accountable for a loss of money or property, the loss must be recovered from that employee unless the Minister of Finance has specifically authorized the public body to waive recovery in accordance with Article 9 of the Financial Administration Proclamation.

፹፬. <u>የዲስፕሊን እርምጃ</u>

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በቂ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ በፌዴራል የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን መመሪያዎች መሠረት ጉድለቱ በሚመለከተው የመንግሥት ሠራተኛ ላይ የዲስፕሊን እርምጃ ይወስዳል።

፪. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የዲስፕሊን እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ሲወስን ፣ እንዲህ ያለው እርምጃ አግባብ ባላቸው ሌሎች ባለሥልጣኖች የሚወሰደውን ማናቸውም ሌላ እርምጃ አይመለከትም።

፹፭. <u>ስለመተካት</u>

ክፍያን የሚጠይቁ የገንዘብ ጉድለቶች ፣ እንደሚተካ ሂሣብ ፣ የገንዘብ ያዥ ጉድለትና በገቢ ላይ የተፈፀመን የማናቸውንም ጉድለት መተካት ሲያስፈልግ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በጽሑፍ የተመደበው ሌላ ሠራተኛ ሲያፀድቀው ለተመሣሣይ ተግባር እንዲውል ከተፈቀደው በጀት መጠየቅ አለበት።

፹፮. <u>የመንግሥት ካዝናዎች</u>

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤት ገንዘብ ያዥ ያለፈቃድ ሲቀር ፣ ሲሞት ወይም ችሎታ ሲያጣ ካዝናው በሂሣብ ሹምና በውስጥ ኦዲት የበላይ ኃላፊ ይታሸጋል።

፪ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በገንዘብ ሚኒስትር መመሪያ መሠረት በካዝናው ውስጥ የሚገኘውን ለመወሰንና ዝርዝሩን ለማዘጋጀት ወዲያውኑ ኮሚቴ ያቋቁማል።

፫. ኮሚቴው ገንዘብ ሚኒስትር የሚያወጣው መመሪያ በሚያዘው መሠረት ምርመራውን ማካሄድና ስላገኘውም ውጤት ሪፖርት ማድረግ አለበት።

፹፯. <u>ጉድለትን ሪፖርት ስለማድረግ</u>

፩. ማናቸውም ጉድለት በመንግሥት ሒሣብ ውስጥ ሪፖርት መደረግ አለበት።

፪. አጠቃላዩ የገንዘብ ጉድለት (አስፈላጊ ሲሆን ግምቱን) ማናቸውንም ተመላሽ ሳይጨምር ጉድለቱ በተፈጸመበት የበጀት ዓመት ሒሣብ ሪፖርት ወይም ጉድለቱ በወቅቱ ሣይታወቅ ሲቀር ተግባራዊ ሊሆን በሚችልበት ዓመት በመንግሥት ሒሣብ ሪፖርት ውስጥ ሪፖርት ይደረጋል።

፫. ጉድለቶች ተመላሽ ሲደረጉ ገንዘቡ በተመለሰበት የበጀት ዓመት የመንግሥት ሒሣብ ሪፖርት መደረግ አለበት።

## ክፍል አሥራ ስድስት
## <u>መዛግብትን ስለማቆየት</u>

፹፰. <u>የጊዜ ገደብ</u>

፩. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለውጭ ኦዲተሮች ለማናቸውም ጉዳይ በመረጃነት የሚያስፈልጉትን የፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብት በቂ ለሆነ ጊዜ ማቆየት አለበት።

፪. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም የፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብት ቢያንስ ለአሥር ዓመት መቆየት አለባቸው።

፹፱. <u>መቆየት ያለባቸው የመዛግብት ዓይነቶች</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፹፰ መሠረት መቆየት ያለባቸው የፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ይጨምራሉ።

84. *Disciplinary Action*

1) Subject to directives issued by the Federal Civil Service Commission disciplinary action shall be taken against the employee(s) involved in the loss, when the head of a public body considers that the circumstances warrant it.
2) When a public body determines that disciplinary action is warranted, such action is distinct from any other measures that may be taken by the appropriate authorities.

85. *Reimbursement*

Losses of money that require a disbursement to reimburse such as imprest funds, cashier shortages and all losses of revenue shall be charged to the appropriation of the related activity, after approval by the head of the public body or such other, senior employee as may be designated in writing by him or her.

86. *Government safes*

1) In the event of the unauthorized absence, death or incapacity of a cashier of a public body the safe shall be sealed by the senior financial officer and the head of the Internal Audit.
2) The Head of the public body shall immediately establish a committee in accordance with directives issued by the Minister of Finance to determine the contents of the safe and prepare a list of them.
3) This committee shall conduct an examination and report its findings as required by directives issued by the Minister of Finance.

87. *Reporting of Losses*

1) All losses must be reported in the Public Accounts.
2) The gross amount of a loss (estimated when necessary) irrespective of any recoveries, is to be reported in the Public Accounts for the fiscal year in which the loss occurred or, when the loss is not discovered in time, in the first Public Accounts in which it is practicable to do so.
3) Recoveries against losses are to be reported in the Public Accounts for the fiscal year in which the amount is recovered.

## *PART SIXTEEN*
## *RETENTION OF RECORDS*

88. *Time Limit*

1) All public bodies shall retain all financial information and records for a length of time adequate to cover all required references to that information by the public body itself or external auditors.
2) Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article all financial information and records shall be retained for a minimum of ten years.

89. *Types of Records to be Retained*

Financial information and records to be retained under Article 89 of these Regulations shall include:

፩. የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና/ወይም ገንዘብ ሚኒስቴር እንዲያፀድቃቸው የቀረቡ ማናቸውም ጉዳዮች፣
፪. እርምጃ መወሰዱን የሚያስረዱ ማናቸውም ማስረጃዎች፣
፫. የፋይናንስ ጉዳዮችን በተመለከተ የተደረጉ መጻጻፎች፣
፬. ማናቸውም ዝርዝር የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችና ደጋፊ ሰነዶች፣
፭. የጥሬ ገንዘብና የደረሰኞች መዛግብትን የመሳሰሉ ማናቸውም መሠረታዊ የፋይናንስ መዛግብት።

፺. <u>የማቆየት ዘዴዎች</u>

የገንዘብ ሚኒስትር ስለፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብቶች አያያዝና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

፺፩. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

1) All submissions for approval to the Ministry of Finance and/or the Council of Ministers,
2) All documents that inform of decisions being taken,
3) All correspondences that relate to finacial matters,
4) All details of financial transactions and supporting documents,
5) All basic financial records such as cash books and records of receipts.

90. *Methods of Retention*

The Minister of Finance shall issue directives that detail the method and length of retention of financial information and records.

91. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa on this 1st day of July 1997.

*MELES ZENAWI*
*PRIME MINISTER*
*OF THE FEDERAL DEMOCRATIC*
*REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE

pro 57 p25/proc